# የፈጣሪ ሕልውና
# በሳይንስ መነጽር

በሃሩን ያሕያ

ትርጉም
ሀምዱ ኢድሪስ

«በሰው ልጆች የፍልስፍና ዘመናት ታሪክ ውስጥ ኒቼ የሚባል ጀርመናዊ ፈላስፋ «አምላክ የሚባለውን ነገር የፈጠሩት ድሆች ናቸው።» ብሎ እንደተናገረ በሌላኛው ቀን ማርክስ የሚባለው የሶሻሊስት መስራች ደግሞ «አምላክን የፈጠሩት ሀብታሞች ናቸው።»ብሎ ነበር። ኒውተን የሚባለው የፊዚክስና የሒሳብ ሊቅ «አምላክ የሚባል ነገር ባይኖር እኛ ሰዎች አምላክን መፍጠር ነበረብን።» በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል። ሃይማኖቶች ያለምንም ማንገራገር «አምላክ አለ! አለ! አለ!» ይላሉ። «የአምላክ ሕልውና በሳይንስ መነጽር» የምትለዋ ይህች መጽሐፍ የዘመናት የህልውና ጥያቄ የሆነውን «የአምላክ መኖር አለመኖር» ጥያቄ እልባት የምትሰጥ ናት ብዬ አምናለሁ።ተርጓሚው ሃምዱ አድራብ ለሃገራችን አንባቢያን በምትመች አኳኋን ተርጉሟታል። መልካም ንባብ።»

አብይ ጣሰው ከትያትር ጥበብ ትምህርት ክፍል

የዘመናችን የፊዚክስ ጥናትና ምርምር ውጤቶች የሆኑ በርካታ መከራዎች ምልከታዎችና ስሌቶች እንዳመላከቱት ፍጥረተ-ዓለም ጅማሬ ያለው መሆኑን አመላክተዋል...

«የእኔ ስራ የገዛውን ዓለም ሚስጢር ማድነቅ ነው» የሚለን የክፍለ ዘመኑ ስመ ገናናው ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን የፊዚክስን ፅንሰ-ሀሳብ ስሌት ካሰላ በኋላ ፍጥረተ-ዓለም ቋሚ ያልሆነና እየተለጠጠ የሚሄድ መሆኑን ደርሶበት ነበር።

ይህ እየተዘረጋጋ ያለው ፍጥረተ-ዓለም (**Universe**) ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ ብንመልሰው በእርግጥ ለዚህ ፍጥረተ-ዓለም መነሻው አንዲት ነጥብ መሆኗን እንረዳለን። ልክ ትልቅ ክብ ነገር እያነሰ ሄዶ ነጥብ እንደሚሆነው ማለት ነው....

ሕይወት በአጋጣሚ የተከሰተ ድንገተኛ ውጤት አይደለም። እንደ ቻርልስ ጋይ ስሌት «አንድ የፕሮቲን ሞለኪውልን ለመስራት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የከዋክብት ክምችት (**Galaxies**) ያስፈልጋል ብሏል።»

ዛሬ ላይ ሳይንስ ይህን የመሰለ ፍጡር በአንድ ምጡቅ የሆነ አካል ካልሆነ በስተቀር ሊሆናወን የማይችል ድርጊት መሆኑን አምኗል። ሳይንስ በፈጣሪ አምላክ የተሸመ ጣኦታትን እያስወገደ ልእለ ኃያል የሆነውን ፈጣሪን እያረጋገጠ ነው.......

ቁሳዊነት (**Materialism**) ቁስ አካል እንደ አምላክ ፈፁማዊ ነገር ሲሆን፣ ምንም ነገር ሳይኖር ቁስ አካል ብቻ እንደነበር ይስማማሉ። ስለዚህም ምክንያታቸው ፈጥረተ-ዓለም ሁሌም ቋሚና የፀና ቁሳዊ ክምችት ነው ብለው ስለሚያስቡ ነበር...

ጠፈር ውስጥ ያለው የሀይድሮጂን ክምችት በከፍተኛ የሙቀት ሀይል ነዶ ወደ ሂሊየም እየተቀየረ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ፍጥረተ-ዓለም ማብቂያ የሌለው ዘለዓለማዊ ነው ይባላልን?...

ዋጋው 9:00 ብር ብቻ

# የፈጣሪ ሕልውና በሣይንስ መነፅር

ዝግጅት፡ በሃሩን ያህያ

ትርጉም፡ ሀምዱ ድሪስ

ነሐሴ 19/99

# ማውጫ


| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| መቅድም | 3 |
| የተርጓሚው መስታወሻ | 6 |
| መንደርደሪያ | 8 |
| ካለ መኖር ወደ መኖር | 15 |
| የፍጥረተ-ዓለሙ መለጠጥና መዘርጋት | 19 |
| በጠፈር ላይ ጨረሮች መነሻ የተገኘ በቂ መረጃ | 23 |
| በጠፈር ውስጥ የሚስተዋለው እጅግ ረቂቅ የሆነ ሚዛናዊ ስርዓት | 27 |
| የቁስ አካል /አተም አፈጣጠር | 30 |
| ከ Big Bang በኋላ | 32 |
| በሰማይና በመሬት ላይ ያሉ ምልክቶች | 34 |
| ሳይንቲስቶች የፈጣሪን መኖር ፍንጭ እያረጋገጡ ነው | 36 |
| ተአምራኛው አካላታችን | 46 |
| የአካላችን አፈጣጠር | 47. |
| አካላችንን የሚከላከል ህብረ-ብሄር ጦር | 49 |
| የሰው ልጅ አእምሮ | 51 |
| የሠው ልጅ አጥንትና ድንቃድንቆቹ | 53 |
| እንስሳትና እፀዋት | 55 |
| የተመጣጠነ ክንፍ | 56 |
| እንገተ-ረጅሙ እንስሳ | 57 |
| የተለያዩ ነገሮችን በመምሰል ራሱን የመከላከል ብቃት | 59 |
| ማጠቃለያ | 61 |

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

All Rights Are Reserved

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

1428 ሂጅራ
1999 ዓመተ ልደት

# መቅድም

በሰው ልጆች የፍልስፍና ዘመናት ታሪክ ውስጥ ከዕለታት በአንድ ዘመን ኒቼ የሚባል ጀርመናዊ ፈላስፋ «አምላክ የሚባለውን ነገር የፈጠሩት ደሀዎች ናቸው» ብሎ እንደተናገረ በሌላኛው ቀን ማርክስ የሚባለው የሶሻሊስት መስራች «አምላክን የፈጠሩት ሀብታሞች ናቸው»ብሎ ነበር።።በሌላኛው ሌላ ቀን ኒውተን የሚባለው የፊዚክስና የሂሳብ ሊቅ «አምላክ የሚባል ነገር ባይኖር እኛ ሰዎች አምላክን መፍጠር ነበረብን»በማለት አስታየቱን ሰጥቷል።።ሃይማኖቶች የለምንም ማንገ ገር «አምላክ አለ! አለ! አለ! ይላሉ።። «የአምላክ ሕልውና በሳይንስ መነጽር» የምትለዋ ይህች መጽሃፍ የዘመናት የህልውና ጥያቄ የሆነውን «የአምላክ መኖር አለመኖር» ጥያቄ እልባት የምትሰጥ ናት ብዬ አምናለሁ።።ተርጓሚው ሃምዱ እድሪስ ለሃገራችን አንባቢ በምትመች አኳኋን ተርጉሟታል።። መልካም ንባብ።።

አብይ ማሰው የቲያትር ጥበብ ተማሪ

ሕይወት የአጋጣሚ ውጤት ለለመሆኑ እንደ ቻርለስ ጋይ ስሌት አንድ የፕሮቲን ሞሉኪውል ለመስራት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የከዋክብት ክምችት (Galaxies) ያስፈልጋል ብሎዋል።።የሚፈጀውን ጊዜ ሲያሰላው አንድ ቁጥርን ዕፈን ከስሩ 263 ($1x10^{263}$) ዜሮዎችን ማስከተል ነው።።

ዛሬ ላይ ሳይንስ ይህን የመሰለ ፍጡር በአንድ ምጡቅ የሆነ አካል ካልሆነ በስተቀር ሊከናወን የማይችል ድርጊት መሆኑን አምኗል።። ሳይንስ በፈጣሪ አምላክ የተሸሙ ጣኦታትን እያስወገደ ልእለ ኃያል የሆነውን ፈጣሪን እያረጋገጠ ነው።።

ቁሳዊነት (Materialism) ርዕዮተ-ዓለም አመለካከት ቁስ አካል ፈፁማዊ የሆነ ነገር ሲሆን፤ ምንም ነገር ሳይኖር ቁስ አካል ብቻ እንደነበር ይስማማሉ።። ምክንያቱም ፍጥረተ-ዓለም ቋሚ የማይለወጥ የፀና ቁሳዊ ክምችት ነው ብለው ስለሚያስቡ ነበር።።

የዘመኑ የፊዚክስ ጥናትና ምርምር ውጤት የሆኑ በርካታ መከራዎች ምልከታዎችና ስሌቶች እንደሚያመለክቱት ፍጥረተ-ዓለም ጅማሬ ያለው መሆኑን ደርሰውበታል።

የባለፈ ዘመኑ ስመ ገናናው ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን የፈለሰፈውን ፅንሰ-ሀሳብ ስሌት ካለ በኋላ ፍጥረተ-ዓለም ቋሚ ያልሆነና እየተለጠጠ የሚሄድ መሆኑን ደርሰበት ነበር።

ይህ እየተዘረጋጋ ያለው ፍጥረተ-ዓለም (Universe) ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ ብንመልሰው በእርግጥ ለዚህ ፍጥረተ-ዓለም መነሻው አንዳች ነገር መሆኑን እንረዳለን። ልክ ትልቅ ኮከብ ነገር እያነሰ ሄዶ ነጥብ እንደሚሆነው ማለት ነው።

« ይህ ሊሆን የማይችልና እንግዳ የሆነው አሁን የምናየው ድንገተኛ የተፈጥሮ ሥርዓት-ጅማሬ ከፍልስፍና አንፃር ጥሩ ስሜት አልፈጠረልኝም» ሰር ፍሬድ ሆሊ

ጠፈር ውስጥ ያለው የሀይድሮጂን ክምችት በከፍተኛ የሙቀት ሀይል ነዶ ወደ ሂሊየም እየተቀየረ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ፍጥረተ-ዓለም ማብቂያ የሌለው ዘለዓለማዊ ነው ይባላልን?

«ከአብይ ፍንዳታ በኋላ ፍጥረተ-ዓለም የመለጠጥ ፍጥነቱ ቅንጣት ታክል ለውጥ ቢያሳይ፦ ሌላው ቀርቶ የአንድ አንድ ቢሊዮንኛ(1/1000 000 000) ሰኮንድ እንኳን ልዩነት ቢያመጣ፦ አንድም በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ የሚኖር ኮከብ እንኳ ባልተመሰረተ ነበር» ከተለመደው ፍጥነት ለቅፅበት ቢዘገይ ሙሉ ለሙሉ በዚያች ቅፅበት እንዳለ ይጠድማል ወይም (collaps) ያደርጋል። በአንጻሩ ደግሞ ጥቂት ቢፈጥን ፍጥረተ-ዓለሙ የጠፈር አካላትን ጨምሮ ዳግም ላይመለሱና ላይገናኙ ሙሉ ለሙሉ ይበታተኑ ነበር። ፕሮፌሰር ፓውል ዴቪስ

ፍጥረተ-ዓለሙ እንደስፋቱ የሰፋ ዓላማ ያለው ነው።» ሮጀር ፔንሮስ

የአንድ ሰው አዕምሮ የመሰብሰብ ስርአት ቢያጥመውና እንደ ኮምፒውተር ፈታታን እንሰራው ብንል እንግሊዝን 13 ጊዜ የሚሰፋ ቦታ አይበቃውም ቢባል ያምናሉን።

እነዚህን እውነታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ብዙ ነገሮችን እንድናስብ ያደርገናል።ለሰብአዊ ፍጡር ስለ ህይወት ያለውን ግንዛቤ መለስ ብሎ እንዲያጤንና ግዴታውንና ተልዕኮውን እንዲገነዘብ ስለሚያስችለው ነው። መልካም ንባብ ተርጓሚው

ዝነኛው (atheist)[1] ፈላስፋ አንቶኒ ፍሊው የሰጠው አስተያየት ደግሞ፡- «ከመጥፎ ነገር ተላቆ ንስሀ መግባት ለነፍስ መልካም ነው፡፡ ስለዚህ ጅማሬውም ንስሀ ነው፡፡ ብልሃተኞቹ አቴይስቶች(ኢ-አማኒያን) በጠፈረተኞቹ ተመራማሪዎች መካከል በተፈጠረው ስምምነት ሊያፍሩ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ተመራማሪዎቹ ቅዱስ ቶማስ በፍልስፍናው የኣረጋገጠውን አመለካከት ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ሰጥተውታል፡፡ እርሱም ምንድነው ከተባለ? ፍጥረተ-ዓለም ጅማሬ አለው የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት የነበረው የፍጥረተ-ዓለም ፍቺ ያለፍፃሜውም ሆነ ያለጅማሬው ፍጥረት ሲሆን ይህ ደግሞ ቀላል አረዳድና ግምት ሲሆን ተራ ግኝትም ነበር፡፡ከዚህ መሰረተ-ሃሳብ የሚገኙ ማንኛውም እውነታዎች አማራጭ የሌላቸው መለኪያዎች አድርገንም እንቀበለው ነበር፡፡እኔ እንደማምነው ይህ ውሳኔ ትክክል ነው እላለሁ፡፡ነገር ግን አሁንም ቢሆን መታሰብ ያለበት ነገር ቢኖር ይሄንን አመለካከት ከBig Bang ንድፈ ሀሳብ እውነታ አንጻር ታሪካዊ ገፅታውን መጠበቁና አቋም መያዙ ቀላልም አይደለም ምቹም አይሆንም»[2] ብሎዋል፡፡

የፊዚክስና የአስትሮኖሚ ጥናት መስራች የነበረው ጆሀንስ ኬ ፕለር በአምላክ ላይ ጠንካራ እምነት እንዳለው ከፃፈው መፅሀፍት ቀንጭበን ስንመለከት፡-«እኛ የስነ ከዋክብት ሊቆች ከሁሉም በተሻለ መልኩ በሳይንስ መፅሀፍቶቻችን የአምላክ ከፍተኛ ክህነት ነን፡፡ በዚህ ላይ ከማንም በተሻለ ብቸኛ ባለመብት እኛው ነን፡፡ ይህም የሚሆነው ለአእምሮዎቻችን ክብር ለመቀዳጀት ሳይሆን ነገር ግን መሆን ያለበት ከዚህ ሁሉ የበላይ ለሆነው ፈጣሪ ክብር ሊባል ነው፡፡»[3] ብሎዋል፡፡

---

[1] በፈጣሪ መኖር የማያምን

[2]. Henry Margenau and Roy Abraham Varghese, eds., *Cosmos, Bios. Theos*, La Salle, IL.: Open Court Publishing, 1992, p. 241

[3]. Henry M. Morris, *Men of Science Men of God*, Master Books, 1992, p.13

# የተርጓሚው ማስታወሻ

ቀደም ሲል «የሕሊና እረፍት» በሚል ርዕስ ከተለያዩ ታዋቂ ግለሰቦች የተወሰዱ በስነ ልቦና ዙሪያ የተዳሰሱ ጭምቅ ሀሰቦችን አካታ የያዘች አጠር ያለች መጽሐፍ አሳትሜያለሁ:: አሁን ደግሞ የታዋቂውን ደራሲ ሀሩን ያህያ "The Existence of God" የተሰኘውን መጽሐፍ «የአምላክ ሕልውና በሳይንስ መነጽር» በሚል ወደ አማርኛ መልሼ ለአንባቢዎች አቅርቤያለሁ:: በመጨረሻም በዚህ ዝግጅት የላሰለሰ ጥረት ላደረጉልኝ ሁሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው:: በተለይም በሀሳብም በማረምም ለረዱኝ አህመዲን ጀበል ፣አብይ ጣሰው ፣ኢስሀቅ እሸቱና ጽሑፉን በኮምፒውተር ለባፈችልኝ እህት አለዊያ ሰዒድ አላህ ምንዳቸውን ይከፈላቸው:: እሚገነ አምባቢያን ለቀጣይ ስራችን ግብአት ይሆነን ዘንድ ማንኛውንም አይነት የእርምትና የማስተካከያ አስተያየት መስጠት ይቻላል::

ተርጂሚው ሀምዱ እድሪስ

E-Hmdu96@Yahoo.com.

MoBIL 0911762123

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

1428 ሂጅራ

1999 ዓመተ ልደት

# መንደርደሪያ

ለአንድ አፍታ በተቀመጣችሁበት ቦታ ሆናችሁ በዙሪያችሁ ያሉትን ነገሮች በሙሉ ተመልከቷቸው «ፈጠራ»መሆናቸውን ይገነዘባሉ። ግርግዳዎቹ፣ ጠረጴዛዎቹና ልብሶቻቸው፣ኮርኒሱ፣ የተቀመጡበት ወንበር አሁን በእጃም ላይ ያለው መጽሐፍ፣ በጠረጴዛው ላይ ያሉት ብርጭቆዎችና በርካታ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ነገሮች እርሶንም ጨምሮ አንዱም ቢሆን በራሱ ብቃትና አስገኚነት ክፍልም ውስጥ አልተከሰተም። ሌላው ቀርቶ የምንጣፎችን የጠርዝ ዘርፎች ብናጤን በአንድ ሠሪ ክሽን ተደርገው የተሸመኑ መሆናቸውን እንረዳለን። በአጋጣሚና እንዲያው በእድል ራሳቸውን አስገኝተዋል አንልም።

ይሄንን መፅሐፍ እያነበበ ያለ አንድ ግለሰብ የሚረዳው ነገር ቢኖር መፅሐፉ ለሆን ዓላማ በደራሲው የተደረሰ መሆኑን ይረዳል። መጽሐፉ በእጁ ሊደርስ የቻለውም በአጋጣሚ ነው ብሎ አያምንም። በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ዲዛይኑ የሳቡትን ቅርፃቅርፅ ቢመለከቱ ወዲያውኑ ቀራጩን ያደንቃሉ። በቀራጩ የተቀመሩ ስራዎች ለመሆናቸውም እርግጠኛ ኖት። አንዱ በሌላው ላይ ተነባብሮ የሚሰራው የብሉኬት ህንፃ አንድ ነገር ይመሰክራል። በአንድ አካል የተለያዩ ሐደቶችን አልፎ በእቅዱ መሰረት እውን እንደሆነ እንደመድማለን። ስለዚህ በየቦታውና ሁኔታው አንድ ወጥ የሆነ ሥርዓት አለ። ይኸስም ይብዛም የዛ ነገር መስራችም ሆነ የበላይ ተቆጣጣሪ አለው።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላቸው የአለማችን ታላላቅ የስልጣኔ አሻራ የሆኑ ግንባታዎችን ሀውልቶችን፣ ቤተ-መቅደሶችን፣ የነገስታት መቃብሮችን፣ ቤተ-መንግስቶችና ቁሻዎች ወዘተ.. ለአብነት ማንሳት ይቻላል፣ የፓሪሱ አይፊል ማማ፣ ታላቁ የቻይና ግንብ፣ የሮማው የመሰብሰቢያ «ፓላሲየም»፣የግብጹ ፒራሚድ፣ ታጅማል

መስጅድ ጨምሮ ሌሎችንም በርካታ ድንቃድንቅ የሆኑ ስራዎች በሙሉ በከፍተኛ ጥበብና ዕውቀት የተገነቡ ናቸው።እነዚህ ሁሉ የተነደፉትና የተገነቡት በመሀንዲሶችና በግንበኞች ለመሆናቸው ግልፅ ነው! የብሪታኒያ ግዙፍ ቅድመ ታሪካዊ ትክል ድንጋዮችም እንዲሁ ቀደም ሲል ስልጣኔዎች እንደነበሩ በተጨባጭ ያረጋግጡልናል።እነዚህ ሁሉ ምሣሌዎች አንድን እውነታ የሚያሣዩ ናቸው።ከነዚሁ ጥንታዊ ስልጣኔዎች ውስጥ የፓሪስ ተምሳሌት የሆነውን የአይፍል ታወር (ማማ) እንደምሳሌ መዘን ስንመለከት፡-

የአይፍል ታወር ግንባታ በ1887 ተጀምሮ ሀያ ስድስት ወራትን ከፈጀ በኋላ በ1889 የተጠናቀቀ ሲሆን 321 ሜትር ርዝመት አለው። ለአርባ አመታት ያህል የዓለማችን ረጅሙ ሠው ሠራሽ ህንፃ በመሆን እንደኘነትን ተቆናጥጦ ቆይቷል። በአይን ሲታይ ቀላል ክብደት ያለው ቢመስልም ግን 9000 ቶን ድረስ ይመዝናል ።ይህንን ሀውልት ለመስራት ብዙ መሀንዲሶችና ሠራተኞች ተሣትፈዋል።እነኚህ ሠዎች ሀውልቱን ሲያቆሙ ማናችንም ብንሆን አላየንም። ነገር ግን በዘመኑ ባንኖርም ብዙ ሠዎች በግንባታው እንደተሣተፉ ግን እርግጠኛ ሆነን መናገር እንችላለን። እስኪ እንዝብልና ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ወደርሶ በመጠጋት «በአንድ መጋዘን የተከማቹ ጥሬ ብረትና የድንጋይ ከሰል ቀልጠ ድንገት በተፈጠረ ፍንዳታ በቅፅበት የብረት ዘንጎች ሆነው እርስ በርስ ተቀንብበረው ፓሪስ የሚገኘውን ዝነኛውን የአይፈል ማማን ቢገነባ ወይም በዕድል ሰሩ» ብሎ ቢነግሮዎት እርሱንና እርሱን እምነው የተቀበሉ ሰዎችን ጤንነት አይጠራጠሩምን?

ማንኛውም ዝርዝር ንድፍም ሆነ ስርአት የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ትልቅም ሆነ ትንሽ በእርግጥ የነደፈው እና የገነባው አካል እንዳለ ያሣያል። ከፍ ብለን ከሄድን ይህ ያለንበት ወሰን የለሽ ፍጥረተ አለም ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያደርገው እጅግ ድንቅ ሚዛንና የተለያዩ

ባህሪያትን የተላበሡት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፍጡራኖች ሁሉ ፈጣሪ የላቸውምን?

እንግዲህ ልብ ይበሉ! በዙሪያችን ያሉት ነገሮች በሙሉ የአጋጣሚ ውጤቶች እንጂ በአምላክ የተፈጠሩ አይደሉም ብሎ መናገር የፓሪሡ አይፍል ማማ በፍንዳታ ነው የተፈጠረው ከማለት የበለጠ አስቂኝ ነገር እንደሌለ ግልፅ ነው:: ይህ ወሰን የለሽ ፍጥረተ-ዓለም የተገነባው ወሰን የለሽ ጥበብና ሀይል አይመስላችሁም? ወይስ ባጋጣሚ የተከሰተ እንክን የለሽ ስራ ነው? መልሱን ለናንተው::

«የሠማያትና የምድር መፈጠር የሌሊትና የቀን መፈራረቅ ሰዎችን የሚጠቅም ነገር (ተሸክማ) ባህር ላይ የምትጓዘው መርከብ አላህ ከሰማይ በሚያወርደው ዝናብ ምድርን ከሞተች በኋላ ህያው ማድረጉ ከርሷም ላይ ተንቀሣቀሽ (ህይወት ያላቸው) ነገሮችን ሁሉ መርጨቱ በሠማይና በምድር መካከል የሚኖረው ደመና ዐዋቂ ለሆኑ ህዝቦች (የአላህን ችሎታና ጥበብ የሚያሣዩ) ምልክቶች ናቸው::» (ቁርአን በቀራ:164)

የአዝጋሚ ለውጥ ፅንስ ሀሳብ (Evolution Theory) የፈጣሪን መኖር ሲያስተባብል ከላይ ከተጠቀሰው ምሳሌ ጋር ፍፁም የሚመሳሰል ነው:: በሁለቱም አስተሳሰቦች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም:: ፅንስ-ሀሳቡ ሕይወት የሌላቸው ሞሉኪዩሎች አሚኖ አሲድን በአጋጣሚ ሰሩ:: አሚኖ አሲድ ደግሞ ለፕሮቲን ንጥረ-ነገር የአጋጣሚ ግኝት ምክንያት ሆነ:: በመጨረሻም ፕሮቲን ሕይወት ያላቸውን ፍጡራንን በተመሳሳይ አጋጣሚ አስገኘ እንደማለት ነው::

ሕይወት ያላቸው ነገሮች በአጋጣሚ የመገኘታቸው እድል ከአይፈል ማማ የመገኘት ዕድል የባሰ እጅግ የተመናመነ ብቻ ሳይሆን የማይታሰብ አመለካከት ነው:: ምክንያቱም አንዲት ህይወት ያላትን ህዋስ ወስደን በዓለም ላይ ካሉ ሰው ሰራሽ ነገሮች ጋር ብናወዳድር ይህ ነው የማይባል እጅግ ውስብስብና ረቂቅ የሆነ ልዩነት በመካከላቸው

እናስተውላለን። አንዳንድ ሰዎች የተፈጠርነው በአጋጣሚ ወይም በእድል አሊያም በተፈጥሮ አማካኝነት ልንፈጠር የቻልነው ይላሉ። እስኪ የሰው ልጅ ባጋጣሚ ሊፈጠር የሚችል ፍጡር ለመሆኑ በሳይንሳዊ መንገድ ለማየት እንሞክር። ከፕሮቲን የተወሰነ ይዘት ያለው እጅግ በጣም አነስተኛ የቆስ አካል ክፍል ሆኖ በህያው ሴል አወቃቀር ውስጥ ዋነኛውን ድርሻ የሚይዘው ፕሮቲን ሞሉኪውል ነው። ይህ የፕሮቲን ሞሉኪውል በውስጡ ካርቦን፣ አክስጂን፣ ነይትሮጂን፣ ሀይድሮጂንና ሰልፈርን ይዘዋል። አንድ ሞሉኪውል ለመስራት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ አተሞች ወይም ቅንጣቶች ያስፈልጋሉ። ማንኛውም የተፈጠር ነገር የተሰራባቸው ነገሮች በግምት 92 የሚደርሱ ነጥረ ቁሶች (Element) አሉ። እነዚህ 92 ንጥረ-ነገሮች በአጋጣሚ ወይም በእድል አምስቱ ተቀናጅተው አንድ የፕሮቲን ሞሉኪውል የመስራት እድል ፓንክ አሊያም በተባለ ሰው ተሰልቶ ውጤቱ ዜሮ ሆኖዋል። ይቺን አንድ የፕሮቲን ሞሉኪውል ለመስራት እንደ ቻርልስ ጋይ ስሌት በሚሊዩን የሚቆጠሩ የከዋክብት ክምችት (Galaxies) ያስፈልጋል ብሉዋል። የሚፈጀውን ጊዜ ሲያሰላው ደግሞ አንድ ቁጥርን ዕፊን ከስሩ 263 $(1x10^{263})$ ዜሮዎችን ማስከተል ነው።

በአንዲት ሴል ውስጥ ምን ያህል የፕሮቲን ሞሉኪውሉች እንዳሉ ያውቃሉ? በሰው ልጆች ውስጥ ምን ያህል ሴል/ህዋስ እንዳለ ያውቃሉ? አንድ ህፃን ሲወለድ ከስድስት ቢሊዩን በላይ ሞሉኪውል ይዞ ይወለደል ።አንድ የፕሮቲን ሞሉኪውል ለመስራት እንኳ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ አመታትን ይፈጃል። ነገር ግን አንድ እናት በዘጠኝ ወር እርግዝናዋ ከስድስት ቢሊዩን በላይ ፕሮቲን ሞሉኪውል የያዘ ህፃን ትወልዳለች።ዛሬ ላይ ሳይንስ ይህን የመሰለ ፍጡር በአንድ ምጡቅ የሆነ አካል ከልሆን በስተቀር ሊከናወን የማይችል ድርጊት መሆኑን አምኖዋል። ሳይንስ

በፈጣሪ አምሳል የተሾመ ጣኦታትን እያስወገደ ልእለ ኃያል የሆነውን ፈጣሪን እያረጋገጠ ነው።

እንዴት በዓለም ላይ የሚታየው የተፈጥሮ ሚዛን በአጋጣሚ ሊመጣጠን ቻለ? ይህ በአይናችን የምናየው ወደር የለሽ ያልተሰመደና በዓይነቱ ልዩ የሆነ የተፈጥሮ ህብርና ስምምነት እንዴት እውን ሊሆን ቻለ? መሰው ፍጥረት-ዓለም ሕልውናውን ወዳስገኘለት አንድ ፈጣሪ እያመለከተ ሳለ አይ! ባጋጣሚ ራሱን ያስገኘና ወፍ ዘራሽ ነው። ብሎ መፈረጅ እጅግ ኢ-ምክኒያታዊ ድምዳሜ ነው።

ያለጥርጥር በያ ቦታው የምንመለከተውን ሚዛን የነደፈና የኛንም አካል ጨምሮ የዚህን ወሰን የለሽ ፍጥረተ-ዓለም ጥጋጥግ ያሉ ነገሮችን የመሰረተና የቀመረ ባለቤት መኖር አለበት።

እና የዚህ ቀመር ፈጣሪ ማን ነው? ማን ነው የምናየውንና የማናየውን እያንዳንዱን ነገር የፈጠረውና የተቆጣጠረው። ይህንን ትንግርት በሙሉ ዕውን ያደረገ ፈጣሪ መቼም ከፍጥረተ-ዓለሙ ቁስ አካል ጋር አብሮ የተገኘ ነው ማለት የማይታሰብ ነው። ምክንያቱም የርሱ ህልውና ከፍጥረተ-ዓለሙ መፈጠር የቀደመ ሲሆን የፍጥረተ-ዓለሙን ፍጥረተ-ዋዜማ ዕውን ያደረገ ነው።ልዕለ ኃያል ፈጣሪ አንድ ነው በርሱም ፍቃድ ሌሎች ሊገኙ ችለዋል። እርሱም መጀመሪያም መጨረሻም የለውም።

ሀይማኖት በምክንያታዊ ፍተሻ መኖሩን የምናረጋግጠውን ፈጣሪያችንን የበለጠ የስተዋውቀናል። በሚሠጠውም ትምህርት የአምላክን ማንነት፣አዛኝና ሩሕሩሕነቱን ፍጥረተ-ዓለሙን ከምንም ማስገኘቱን የስገነዝበል። በእርግጥ አብዛኛዎቹ ሰዎች ብዙ ግዜ ይሄንን እውነት የመረዳት እድል አላቸው።ነገር ግን ይህንን ታላቅ እውነታ ወደ ጎን ሲሉት ይስተዋላሉ። በእንፃሩ አንድ ሰዓሊ የሰራውን ስዕል አሊያም አንድ ቀለም ቀቢ የቀለመውን ግርግዳ አይተው ይደነቃሉ። ጥበበኛውንም በማያምረው ስራው አልቀው ያዩታል። ግና እነዚህ ሰዎች

በተፈጥሯዊ ዓለም ውስጥ ተንሰራፍተው የሚገኙትን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ፍጥረታትና የሕብረ-ቀለማት ውህድ ድንቃድንቆች ባለቤትነት እውነታ በአንግሩ እናሳ ግምትና እውቅና ሊሰጧቸው ይስተዋላሉ።

ለሁሉም ነገር ባለቤት እንዳለው ከተረዳን፡- ፈጣሪ ደግሞ ሁሉንም ጠቅልሎ የሚገዛ የሁሉም ነገር ባለቤት ነው። እርሱም የዚህ ድንቅና ውብ ዓለም ባለቤትና ገዥ ነው። በእውነቱ ከሆነ የፈጣሪን መኖር ለማወቅ፤ እሊያም ለማፅደቅ ምንም ውስብስብ ጥናትና ምርምር አይጠይቅም።እንድ ግለሰብ ይህ በገሀዱ ዓለም የምናየው ሁሉ መረጃ ባይቀርብለት እንኳ ከተወለደበት ማግስት አንስቶ በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲቆይ ቢደረግ እንኳ ስለፈጣሪ መኖር ወሰን የለሽና ከበቂ በላይ መረጃ ማግኘት ይችላል። የሰውነታችን አካላት ቁጥረን የማንዘልቀውና በአያሌ የኢንሳይክሎፒዲያ ጥራዞች ፅፈን የማንጨርሰው ፈጣሪን የማግኛ ቁልፍ መረጃዎችን ይዞዋል። ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም ብለን ብናስብና ከፊት ለፊታችን ለምናገኛቸው እውነታዎች የባለቤትነት መልስ መመለስ ብንጀምር በርግጥም የፈጣሪን መኖርና ልዩ ሥራውን ያመላክቱናል።ይህ ሁሉ ስርዓትና ተፈጥሮአዊ ህግም በርሱ ቁጥጥር ስር ለመሆኑ እርግጠኞች እንሆናለን።

ዓለም በአያሌ ህይወት ባላቸው ነገሮች የተሞላች ናት።ሕይወት ያላቸው ነገሮች በመሬት ላይ በየሚሊሜትር ካሬ መሸጎውና ተቸምችመው ይገኛሉ። በሰው አይን ሊታዩም ላይታዩም ይችላሉ።ከባለአንድ ህዋስ እስከ ትላልቅ እፅዋት።ከደቂቅ እስከ ግዙፍ የባህር እንስሳት ከአእዋፍ እስከ ሰብአዊ ፍጡር የተሞላች ናት። ለአብነት ያህል አንድ እፍኝ አፈር ዘግነው ቢመለከቱ በውስጡ ባለዘርፈ ብዙና የተለያዩ በህሪ የላቸው ፍጥረታትን ያገኛሉ። በምንተነፍሰው አየር ውስጥ ፤ ሌላው ቀርቶ በገዛ ቆዳችን ስር ገና ስማቸውን እንኳ ሰምተን የማናውቃቸው ብዙ ሕያው ፍጥረታት በጥገኝነት ይኖራሉ። እነዚህ ጥቃቅን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ባክቴሪያዎችና ባለአንድ ህዋስ የሆኑ

ፍጥረታቶች በትላልቅ እንስሳት አንጀት ውስጥ የስራዓተ-ልመት ሂደት (digestive system) በማገዝ አንጀት ውስጥ አብሮ በጥገኝነት ይኖራሉ:: በዓለም ላይ የእንስሳት ብዛት በብዙ እጥፍ ከሰው ልጅ ብዛት ይበልጣል::በአንፃሩ የእፅዋትን ሁኔታ በዓለም ላይ ስናጤን አንድ ነጥብ የምታክል ቦታ እንኳ ያለ ሕይወት ባዶ አለመሆኗን እንረዳለን::እንግዲህ እነዚህ ህይወት ያላቸው ህልቆ መሳፍርት በሚሊዮን ኪሎ ሜትሮች በተለየ መልኩ ህብረት ፈጥረው ተንሰራፍተው ይኖራሉ:: በተለያየ አኗኗርና በተለያዩ አስተጥዖአ ለብዙሃ-ህይወት እያበረከቱ ሚዛኑን ጠብቀው ይኖራሉ::

ታዲያ ይሄ ሁሉ ብዙሃ-ህይወት እንዲያው በአጋጣሚና በእድል ያለ አላማና ግብ እንዲሁ የተገኘ ነው ብሎ መናገር ምክኒያተ- ቢስነትና እብደት ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ሊባል ይችላል? በራሱ ጥረትና ምርጫ ወደዚህች ዓለም የመጣ ህይወት የለም::በአንፃሩም በገጠመኝ እንደዚህ ዓይነት የተሳሰረና የተወሳሰበ ስርዓትና ሚዛን በጭራሽ ሊገኝ አይችልም:: እነዚህ መረጃዎች ወደ አንድ ድምዳሜ ወይም ማጠቃለያ ያደርሱናል::ይህ ፍጥረተ-ዓለም የሚመራው በእቅድና በጥበብ መሆኑን ያሳያል:: ታዲያ የዚህ ሁሉ ቅንብር ባለቤት ማን ነው? በእርግጠኝነት ከዚህ ስርአት በስተጀርባ ያለው ገዥ አንድም ሕይወት ካላቸውና ከሌላቸው ነገሮች መካከል ነፃ ነው::

እነዚህ ሁሉቱም ቢሆኑ የዚህ ዓለም ሕብረትና ትስስር ስርዓቱን መጠበቅና ማከናወን አይችሉም::ስለዚህ ፈጣሪ መኖሩን በነዚህ ስፍር ቁጥር በሌላቸው ህልቆ መሳፍርት ራሱን ይገልፅልናል::በርግጥ ይሄንን ገሀድ የወጣ እውነታ በዓለም ላይ ማንም ግለሰብ ቢሆን ከልቦናው እያስተባበለውም::ምንም እንኳ በምላሱ ቢያስተባብልም ቁራአን እንደሚለው:-

«ነፍሶቻቸው እውነት መሆናቸውን በጽኑ እያመኑ በማስተባበልና በኩራት (በደለኞችና ትዕቢተኞች በመሆናቸው ሳቢያ) አስተባበሏቸው።» (ቁርአን 27:14)

ልቦና የማይክደው እውነታ መሆኑን ቁርአን ያወሳል። ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀውም ቀም ብለን እውነታውን እንድንናስተውል ነው።አንዳንድ ሰዎች ከዚህ እውነታ ራሳቸውን ሲያሸሹና ልቦለዳቸውን የሚከተሉ ሲሆኑ፡-ሌሎቹ ደግሞ ሆንብለው ለዕውነታው ምላሽ ሳይሰጡ ስሜት-ድንዙዝ ይሆናሉ። ይባስ ብለው ከዚህ እውነታ ተቃራኒ የሆነ አመለካከት መስርተው በቅዥት ዓለም ሲኖሩ ይስተዋላሉ።በዚህም ምክኒያት ብዙ ሰዎች ሀቅን ትተው ስሜታቸውን እንዲከተሉ ተደርገዋል። ያም ሆነ ይህ በዚህች አጭር መፅሐፍ የተለያዩ አንኳርና ወሳኝ ትንታኔዎችን ታመላክታለች ተብሎ ይታመናል።

በመጨረሻም ይሄንን መፀሐፍ የምታነቡ ሰዎች የፈጣሪን የመኖር እውነታ ከዚህ ማለቂያ የለሽ መረጃ ተንተርሳችሁ ለህልውናው እውቅናና የምስክርነት ቃላችሁን እንድትሰጡት የታሰበ ሲሆን በአማክኒዩ (LOGIC) እንድታረጋግጡና፡- እርሱም የዚህ ስርዓተ የበላይ ገዥ ተንከባካቢና አስተናባሪ መሆኑን ለማሳየትና ለማሳወቅ የመንደርደሪያ ሀሳብ ነው።ከዚህ የክህደት ጥፋት አእምሮ ላለው አጋዥ መልዕክት እንዲሆነው፤ ተዘናግቶ እንደሆነ ለማንቃት፤የረሳ ከሆነ ለማስታወስ፤ የማያውቅ ከሆነ ለማሳወቅ፤ይህንን ቃላቅ ሰጦታ ጀባ እንላለን።

## ካለ መኖር ወደ መኖር

የዚህ ወሰን የለሽ ፍጥረተ-ዓለም (Universe) ጅማሬና አመጣጥን ስንመለከት። ፍጥረተ-ዓለም (Universe) ወዴት እያመራ ነው? እንዴት ነው ሕግጋቶቹ የሚጠበቁትና ሚዛናዊ በሆነ አኳኋን የተመጠኑት? የሚሉ ርዕሶችን ያካተተ ነው። ለክፍለ ዘመናት ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎችን ሲያመራምር ቆይቶዋል። በነዚህ ርዕሶችም መላምታቸውን ሰንዝረዋል።

ጥቂት የማይባሉ ንድፈ-ሀሳቦችንም አስቀምጠዋል::ለአብነት ያህል ፍጥረተ ዓለም ወሰን የለሽ ስፋና ጅማሬም ሆነ መጨረሻ የሌላውና ሁሌም የሚኖር ዘውታሪ " Static universe model" ቋሚ የፍጥረተ-ዓለም ሞዴል ተብሎ የሚጠራው መላምት እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ገና የቆየ የዩኒቨርስ ንድፈ-ሀሳብ ነበር::

የፈጣሪን የመኖር ሕልውና ያስተባበሉት የቁሳዊ ፍልስፍና አራማጅ የነበሩት ካርል ማርክስ ከላይ ያየነውን ጽንሰ-ሀሳብ ለቁሳዊ ርዕዮተ-ዓለም መነሻ ሆኖዋቸዋል:: ምክንያቱም ፈጥረተ-ዓለም ቋሚ የማይለወጥ የፀና ቁሳዊ ክምችት ነው ብለው ስላሰቡ ነበር::ቁሳዊነት (Materialism) ርዕዮተ-ዓለም አመለካከት ቁስ አካል ፊፀማዊ የሆነ ነገር ሲሆን፤ ምንም ነገር ሳይኖር ቁስ አካል ብቻ እንደነበር ይስማማሉ:: የዚህ አስተሳሰብ መሰረቱም ከጥንታዊ ግሪክ ፍልስፍና የተወሰደ ሲሆን፤ እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ድረስ በምዕራቡ ዓለም ተቀባይነት ያገኘ ንድፈ-ሀሳብ ነበር::

የዚህ አመለካከት መሰራች የነበረው ካርል ማርክስ ቁስ (matter) ዋንኛው የፍልስፍና ዘዬው ነበር:: ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሰፍኖ የቆየው " Static universe model" ሞዴል ተንተርሶ የተገነቡ የቁሳዊ ፍልስፍና ርዕዮተ-ዓለም አመለካከት ሲሆን፤መሰረቱም ከግሪክ ቁሳዊ ፍልስፍና ሲሆን ዲያሌክቲዊ ቁስ-አካላዊነት የሚል ስያሜ ተሰጥቶት በካርል ማርክስ አማካኝነት ሰፊ ተቀባይነት አግኝቶዋል:::ጆርጅ ፓሊዘር ለዚህ ቲዎሪ መሰረት የሆነው አመለካከት ከየት እንደመጣ የጻፉ ሲሆን (Principes fondametaux de philosophie) በተሰኘው መፀሀፋቸው ፍጥረተ-ዓለምን አስመልክተው ከጻፉት ውስጥ:-

*«ፍጥረተ-ዓለም የሚፈጠር ነገር አይደለም»* የሚል ይገኝበታል ለዚህም ምክንያታቸው

*«ይህ እንዲህ ከሆነ ፍጥረተ-ዓለም በቅጽበት በፈጣሪ የተፈጠረና ካለመኖር ወደ መኖር የመጣ ነው ልንል ነው። ይህን ለመቀበል በመጀመሪያ ደረጃ ፍጥረተ-ዓለሙ ከመፈጠሩ በፊት አስቀድሞ የነበረውን ጊዜ ማየትና አንድ ነገር ካልነበረበት ተገኘ የሚለውን አባባል መቀበል ያሻናል።እነዚህን ጉዳዮች ደግሞ ሳይንስ የማይቀበላቸው ነገሮች ናቸው።ይላሉ።»[1]*

ፖሊዘር እንዳብራሩት ፍጥረተ-ዓለም ከአንድ ከሌላ ነገር አልተፈጠረም ለማለት የቻሉት በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበረው“ Static universe model” *በመንሳት* የወሰዱት ሳይንሳዊ መላምት ነው። ነገር ግን 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያፈራው የቴክኖሎጂና የሳይንስ ዕምርታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ስለነበር፡- ይህ ለቁሳዊነት መሰረት የሆነው ኋላ-ቀር ፅንሰ-ሀሳብ በማለት አጣጥሎታል።

የዘመኑ የፊዚክስ ጥናትና ምርምር ውጤት የሆኑ በርካታ ሙከራዎች ምልክታዎችና ስሌቶች እንደሚያመለክቱት ፍጥረተ-ዓለም ጅማሬ ያለው መሆኑን ደርሰውበታል። የተፈጠረውም ከምንም ተነስቶ በተፈጠረ ግዙፍ ፍንዳታ መሰረት ዕውን ሊሆን የቻለ ነው።ስለሆነም ፍጥረተ-ዓለሙ ጅማሬ አለው።ጠፈር ካለምንም ሊገኝ ቻለ። እሱም «መፈጠር» ነው የሚለውን ያሲዛል። በሌላ አባባል አንድ የተፈጠረ ነገር ግኝት ከሆነ፡- ከግኝት ዋዜማው በፊት አንዲት እርምጃ ወይም ስከንድ ወደ ኃላ የማይገኝበት ድንበር ጋር መፋጠጥ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ ከበስተጀርባው የፍጥረተ-ዓለሙን ሕልውና ያስገኘ አንድ አካል መኖር አለበት። ምክንያቱም ካለአስገኝ መገኘትን የሰው ህሊና ሊቀበለው የማይችለው ነገር ነው።

---

1. **George Politzer,** ***Principes Fondamentaux de Philosophie,*** **Editions Sociales, Paris, 1954, p. 84**[4]

ቆም ብሎ የሚያስብበት እድል እስካለገኘ በቀር የሰው ልጅ በተግባር ከማይቀበላቸው እውነታዎች ጋር እየተፋጠጠ ነው። ፍጥረተ-ዓለሙ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት ማለት ሁለት ነገሮችን አዳቅሎ አንድ አዲስ ግኝት ከማግኘት የተለየ ጉዳይ ነው። የተለያዩ የቴክኖሎጂ ግኝቶች እንደሚፈበረኩት ዓይነት አይደለም።ይህ ሁሉ ፍጥረት የፈጣሪ ልዩ ምልክት ናው። እርሱም ከ ሀ እስከ ፐ ያለውን አሟልቶና አጣምሮ ሁሉንም በየደረጃው ያስገኘ ነው።እነዚህ ፍጥረታት የቀድሞ ምሳሌ ሳይኖራቸው፣ ሌላው ቀርቶ ስለቁስ ቦታና ግዜ ፅንሰ-ሀሳብ ቅደመ ታሪክ ሳይኖራቸው፣ በመቅፅበት ተፈጥሯል። የፍጥረተ-ዓለሙ ሕልውና ካለመኖር ወደ መኖር መምጣት ስለመፈጠሩ ታላቅ ምስክር ነው። እነዚህን እውነታዎች ግምት ውስጥ ስናስገባ ብዙ ነገሮችን እንድናስብ ያደርጉናል።

ይህ ሰው ለሚባለው ፍጡር ስለ ህይወት ያለውን ግንዛቤ መለስ ብሎ እንዲያጤንና ግዴታውንና ታልዕኮውን እንዲገነዘብ ስለሚያስችለው ነው። ይህ ጉዳይ ለምን በሳይንሱ ማህበረሰብ አካባቢ ችላ እየተባለና ትኩረት የተነፈገው የፍጥረት እውነታ ሲሆን።ግና አንዳንድ ሳይንቲስቶች በጉዳዩ ላይ ብዙ መረጃዎች ግልፅ ሳይሆንላቸውና የተሟላ ተጨባጭ እውነታ ለይ ሳይደርሱ እውነታውን ችላ ብለዋል።በተጨባጭ የሚታዩት ሳይንሳዊ መረጃዎቻቸው የፈጣሪን መኖር የሚያረጋግጡ መሆናቸውን እየመሰከሩ የሳይንቲስቶቹ ተጨባጭ ድምዳሜ ላይ አለመድረስ በሰው ሕሊና ላይ መምታታትን ፈጥሯል። ሳይንሳዊ መረጃዎች በራሳቸው የፍጥረትን ሙሉ ዕጣ ፈንታ በራሰቸው ፅንስ ሀሳብ ሊገነባ ችሏል።ይሄንን ሳይንሳዊ እውነታ የፍጥረተ-ዓለም የዕድገት ሒደትና አመጣጥን በተመለከተ ከተሰጡት ትንታኔዎች በጥቂቱ ለማየት እንሞክር።

# የፍጥረተ-ዓለሙ መለጠጥና መዘርጋት

በ1929 አሜሪካዊው የስነ ክዋክብት ተመራማሪ ኤድዋርድ ሀብል በካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ በማውንት ዊልስን በሚገኘው ግዙፍ የምልከታ ጣቢያ ባደረገው የምልከታ ጥናት፡፡ በስነ-ክዋክብት(astronomy) ጥናት ዘርፍ ታሪክ! እጅግ ወሳኝና አስፈላጊ የተባለውን ግኝት አግኝቷል፡፡በግዙፍ ቴሌስኮፕ ባደረገው የከዋክብት ምልከታ፡- የከዋክብቱ ህብረ ቀለማት (Spectrum) ብርሃን ቀይ ቀለም መጨረሻው ላይ የመለወጥ ባህሪን ያሳያል፡፡ይህም አንድ ወሳኝ ፍንጭ አመላከተ፡፡ ይህ የብርሃን ሽግግር በቀጥታዊ ተዛማጅ ንፅፅር ሲዛመድ ክዋክብቱ ከመሬት እየራቁ የሚሄዱ መሆናቸው ለማወቅ አስችሎዋል፡፡

ይህ ግኝት አሁን ላለንበት ዘመን ታላቅ ሳይንሳዊ እምርታና መሰረት ጥሏል፡፡ ምክንያቱም በፊዚክስ ሕግ እንደተረጋገጠው የህብረ-ቀለማት ብርሃን ተሸካሚ የሆነው አመልማሎ! ብርሀኑ በምልከታ ወቅት ሀምራዊው ቀለም የመቀየር ባህሪ ካሳየ የሕብረ ቀለሙ ብርሃን ተሸካሚ ከሆነው አመልማሎ! ብርሃኑ እየራቀ በመሄድ ላይ መሆኑን ሲያሳይ ወደ ቀይ ህብረ ቀለም እየተጠጋ ይሄዳል፡፡ በሀብል የምልከታ ወቅት የከዋክብቱ የብርሃን ቀለማት ወደ ቀይ የብርሃን ቀለም የመቀየራቸውን ግኝት ተደረሰበት፡፡ ይህ ደግሞ በሌላ አባባል ከዋክብት በቀጥታ ከኛ እየራቁ መሆናቸውን ነው፡፡ ብዙም ሳይቆይ ሀብል ሌላም ግኝት አገኘ፡፡ ክዋክብቱ እየራቁ ያሉት ከመሬት ብቻ ሳይሆን እርስበርሳቸው እየተራራቁ መሆኑም አረጋገጠ፡፡ የጥናቱ ድምዳሜ እንደሚያመለክተው ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ ያለ ነገር በቀጥታ እየሰፋና እየተለጠጠ መሆኑ ተደረሰበት፡፡ ይሄንን ሀሳብ በተሻለ መልኩ ለመረዳት ፍጥረተ-ዓለሙን እንደፊኛ አድርገን እንውሰደው፡፡ ፊኛው በአየር በተሞላ ቁጥር እየተለጠጠ ይሄዳል፡፡ በሌላ አባባል የፊኛው መጠን ዙሪያ (ግርግዳ) እየሰፋ

እየተራራቀ ይሄዳል:: ስለዚህ በተመሳሳይ አማክንዩ በጠፈር ውስጥ ያሉ አካላትም እየተራራቁ ይሄዳሉ ማለት ነው::

የዚህ ፅንሰ-ሀሳብ እውነታ ቀደም ብሎ የተረጋገጠበት ሁኔታም ነበር:: የክፍለ ዘመኑ ስመ ገናናው ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን የፊዚክስን ፅንሰ-ሀሳብ ስሌት ካሰላ በኋላ ፍጥረተ-ዓለም ቋሚ ያልሆነና እየተለጠጠ የሚሄድ መሆኑን ደርሶበት ነበር:: ነገር ግን በወቅቱ ገና የቆየውን" Static universe model" ብዙ ድጋፍ ስለነበረው ላለመቃወምና ንድፈ-ሀሳቡን ድጋፍ ላለማሳጣት ተገዶዋል:: ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ አንስታይን እቋሙን እንዲህ በማለት ይፋ አደረገ «ለብዙ ጊዜያት የቆየ ታላቅ ስህተት» ወዲያውኑ በሆብል የምልከታ ጥናት ፍጥረተ-ዓለም (Universe) እየሰፋ መሆኑን ተረጋገጠ::

ዋናው ነገር የፍጥረተ-ዓለም እየተለጠጠ መሄድ ከፍጥረተ-ዓለም መገኘት ጋር ምን ያገናኘዋል? ትሉ ይሆናል:: ይህ እየተዘረጋጋ ያለው ፍጥረተ-ዓለም (Universe) ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ ብንመልሰው በእርግጥ ለዚህ ፍጥረተ-ዓለም መነሻው አንዲት ነጥብ መሆኗን እንረዳለን:: ልክ ትልቅ ክብ ነገር እያነሰ ሄዶ ነጥብ እንደሚሆነው ማለት ነው:: በዚህ ስሌት መሰረት ይህቺው «ነጠላ ነጥብ» የፍጥረተ-ዓለሙ መላ ቁስ (matter) ዜሮ ምድገት (volume) ሲሆን ወሰን የለሽ እፍገት(Density) ይኖራታል:: ስለዚህ ፍጥረተ-ዓለሙ ሊከሰት የቻለውም በዚህች ዜሮ ምድገት ባላት የአንዲት ነጠላ ነጥብ ኃያል ፍንዳታ ለፍጥረተ-ዓለሙ መነሻ ብስራተ-ዋዜማ ሆኗል:: ይህ ታላቅ ፍንዳታ (explosion) በሳይንሳዊ አጠራር Big Bang (ሕብይ ፍንዳታ) (ታላቁ ፍንዳታ) በመባል ይታወቃል::

«ዜሮ ምድገት» ለሳይንሳዊ ፅንሰ-ሀሳብ ገለጻ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን: «ካለምንም» የሚለውን ሀሳብ የወከለ ቃል ነው:: ይህም ከሰው ልጅ የግንዛቤ አድማስ ውጭ ነው:: «ዜሮ ምድገት ያላት ነጥብ» ተብሎ ሲገለጽ ምድገት (Volume) የሌላት ዜሮ ማለት «ምንም አለመኖር» እንደማለት ነው:: ስለዚህ ፍጥረተ-ዓለም እውን የሆነው ካለምንም ነገር ማለት ሲሆን :: በሌላ አባባል «የተፈጠረ» የሚለውን ያመላክታል::

ስለዚህ በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ ያሉ አካላት በሙሉ መነሻቸው የአንዲት ቅንጣቢ አሊያም ቁራጭ መከፋፈል ውጤት ነው:: ይህ ታላቅ

እውነታ በቁርአን ውስጥ ከክፍለ ዘመናት በፊት የፍጥረተ-ዓለም ፅንሰ-ሀሳብ እውቀት ባልዳበረበት በአረቢያ ፔንሱላ እንደሚከተለው ተጠቅሶ መገኘት እጅግ ይገርማል፡፡

«እነዚያ የካዱት፡- ሰማያትና ምድርን የተጣበቁ እንደነበሩና እኛ እንደነጣጠልናቸው አያዩምን? ሕይወት ያላቸውንም ነገሮች ሁሉ ከውሃ ፈጠርን፡፡ (ይህን ሁሉ ጥበብ እያዩ) አያምኑምን?» (ቁርአን 21:30)

በጥቅሱ እንደተብራራው ሁሉም ነገር «ሰማያትን ምድርን ጨምሮ የተፈጠሩት ከዚህችው ባለአንድ ነጥብ ፍንዳታ አማካኝነት ነው፡፡ አሁን ላለው ፍጥረተ-ዓለም መስፋትና ቅርፅ መያዝ መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡ የቁርአኑን ጥቅስ ከአብይ ፍንዳታ ንድፍ ሀሳብ ሲነፃጸር ፍፁም ስምምነት አላቸው፡፡ ነገር ግን የ Big Bang ንድፍ ሀሳብ የታወቀው በቅርብ ጊዜ ማለትም አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነው፡፡ ስለፍጥረተ-ዓለም (Universe) አፈጣጠር የተገለጸ የቅርብ ግዜ የሳይንስ ዓለም እውነታ ሲሆን ፍጥረተ-ዓለሙ ካለምንም መገኘቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የዚህ ግኝት መሰረታዊ እውነታ የታወቀው አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ሳይሆን፡፡ ፈጣሪ አምላክ በላከው መለኮታዊ ራዕይ ከ1400 ዓመታት በፊት እንዲህ በማለት ገልፆታል፡፡

«ሰማይንም በኃይል ገነባናት፡፡ እርሷንም በማስፋት ላይ ቻዮች ስንሆን በእርግጥም ችሎታችን ወሰን የለሽ ነው» (ቁርአን 51:47)

አብይ ፈንዳታ(Big Bang) ሌላ አማራጭ አለውን? ከላይ በግልፅ እንዳየነው ካለምንም ነገር አብይ ፍንዳታ ለፍጥረተ-ዓለም ምስረታ ወይም መፈጠር ሰበብ ሆኗል፡፡ በሌላ አገላለፅ በአምላክ የተፈጠረ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የስነ-ፈለክ ተመራማሪዎች (astronomers) የቁሳዊ ፍልስፍና ሕልውናን ለመጠበቅ የራሳቸውን መሰረታዊ የርዕዮተ-ዓለም ፅንፈኝነትን ለማራመድ ሲሉ የአብይ ፍንዳታ ንድፈ-ሀሳብ ተግባራዊና ገቢራዊ ላለመድረግ አንገራግሯል፡፡ ለዚህም ዋንኛ ምክንያት የቁሳዊ

ፍልስፍናና የፊዚክስ መሁር የነበረው አርቱር ኢዲንግተን እንደሚከተለው ተገልጾዋል

፡ *ይህ ሊሆን የማይችልና እንግዳ የሆነው አሁን የምናየው ድንገተኛ የተፈጥሮ ሥርዓተ-ጅማሬ ከፍልስፍና አንፃር ጥሩ ስሜት አልፈጠረልኝም*[3] ሰር ፍሬድ ሆሊ በአብይ ፍንዳታ ፅንሰሀሳብ ከተማረኩት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን በያዝነው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ቀደም ብሎ፤ ሆሊ " Static universe model" ሲያሞካሽ፤ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበረው «የማይቀየር (ቋሚ) ፍጥረተ-ዓለም ሞዴል» ጋር ተመሳሳይ አቋም ነው *«ፍጥረተ-ዓለም ወሰን የለሽ ዘለኣለማዊና ጅማሬም ሆነ ፍፃሜ የሌለው ነው፡፡»* በማለት ያምን ነበር፡፡ በወቅቱ የቁሳዊ ፍልስፍና ርዕዮተ-ዓለምን የመደገፍ ብርቱ ፈላጎት ነበረው፡፡ በዚህም ምክንያት፡- ሙሉ ለሙሉ ከአብይ ፍንዳታ ፅንሰ-ሀሳብ ማለትም ፍጥረተ-ዓለም (Universe) ጅማሬ እንዳለው ካረጋገጠው ፅንስ ሀሳብ የተለየ አቋም ነበረው፡፡

Static universe model አቀንቃኞችና ደጋፊዎች የBig Bang ንድፈ-ሀሳብ በመቃረን ለተወሰኑ አመታት በአቋማቸው ቢገፉም ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምሩ ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡1948 ጂአርጅ ጋሞቭ አብይ ፍንዳታን በተመለከተ ሌላ ሀሳብ አመጣ፡፡

*«ፍጥረተ-ዓለሙ በቅጽበት የተመሰረተው በድንገተኛ ፍንዳታ ከሆነ ከፍንዳታው የፈነጠቀ የጨረር ቅሪት አካል መኖሩ የግድ ነው፡፡ በፍንዳታው ወቅት የፈነጠቁ የጨረር ፍንጣቂዎች በመላው ፍጥረተ-ዓለም በአንድ ወጥ የተሰራጩ ናቸው»* ብሎ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ከሁለት አስርተ አመታቶች በኋላ የጋሞቭ ሀሳብ ተረጋገጠ፡፡

---

[3] Recounted in Jaki, S. (1980) *Cosmos and Creator*, Regnery Gateway, Chicago

# በጠፈር ላይ ጨረሮች መነሻ የተገኘ በቂ መረጃ

በ1965 አርኖ ፔንዚያ እና ሮበርት ዊልሰን የተባሉ የጠፈር ተመራማሪዎች ከጋሞቭ ጨረሮች ጋር በተያያዘ ያደረጉት የምርምር እምረታ እስካሁን ድረስ ለምርምሩ ግብዓት ሆኖዋል:: ለሙከራ የወሰዷቸው ጨረሮችም «cosmic background radiation» ሲሆን ከየትኛውም ከአንድ ከሚመነጭ የጨረር ዓይነት ጋር ገለልተኛና ተመሳሰይ ሳይሆን በጠፈር ውስጥ የተሰራጨ እንጅብራቂ ጨረር ሲሆን የዚህ ብርሃን ፈንጣቂ ምንጭ ጨረሮች የአብይ ፍንዳታ (Big Bang) አስተጋቢ ማሚቶ ናቸው የሚል ግምት ተሰቷል:: ይሄንን ሀሳብ ካፈለቁ በኃላ እስካሁን ድረስ የሚደረጉት ሳይንሳዊ ሙከራዎችም የሚያረጋግጡት ይህኑን ግኝት ነው:: ሁለቱ ተመራማሪዎች በግኝታቸው የኖቬል ሽልማት ተሸላሚ ሆኖዋል::

በ1989 የአሜሪካ የጠፈር ምርምር ጣቢያ(NASA) የጠፈር ላይ ጨረሮችን መነሻ የምታስስ (COBE) የተባለች ሳተላይት ወደ ሀዋ ልኮ ነበር :: የተልኮዋ አላማ በጨረሮች መነሻ ላይ መረጃ ለማሰባሰብ ነበር:: ሳተላይቷ በተገጠመላት የመረጃ ማስተላለፊያ ስሌዳ ለስምንት ደቂቃ የተቀበለችውን የጨረር መጠን ከፔንዚያና ዊልሰን የጨረር መጠን ዘገባ ጋር የሚስማማ ልኬት ነበር::

በተጨማሪም ይቺው (COBE) ሳተላይት ቀሪውን የአብይ ፍንዳታ ፍንጥቅጣቂ ጨረር ጠቁማለች:: ይህ አጋጣሚ እስከ ዛሬ ከተደረጉ የስነ-ከዋክብት ጥናትና ምርምር ቀዳሚው የተባለው ግኝት ሲሆን የBig Bang ፅንስ ሀሳብን የሚያረጋግጥ ሆኖ ተገኝቶዋል:: የመጀመሪያዋ COBE ሳተላይት የBig Bang ስሌታዊ እውነታን የማረጋገጥ ታልዕኮዋን ከተወጣች በኃላ:: ለቀጣይ ምርምር ሌላ COBE2 የተባለች

ሳተላይት ተልካለች:: በመሆኑም ተጨማሪ መረጃዎች ወደፊት እንደሚገኙ ተስፋ አለ::

የሚካሄደው ምርምር በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ ባለው የሃይድሮጂንና የሒሊየም አንጻራዊ መጠን ተንተርሶ ነው:: ገና ከጅምሩ ጥናቱ እንደሚያመለክተው በንድፍ ሀሳቡ ስሌት መሰረት በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ ያሉት የሀይድሮጂንና የሒሊየም መጠን ከአብይ ፈንዳታ በኃላ በቀረው አንጻራዊ መጠን ምርምሩ ይካሄዳል:: ይህ ለውጥ ለ" Static universe model" አመለካከት ትልቅ ፈተና ነበር:: ምክንያቱም ፍጥረተ-ዓለም ዘልዓለማዊና ጅመሬ የለውም የሚል ድምዳሜ ያሳለፈ ቢሆንም ጠፈር ውስጥ ያለው የሀይድሮጂን ክምችት በከፍተኛ የሙቀት ሀይል ነዶ ወደ ሂሊየም እየተቀየረ ነው:: ይህ ሆኖ ሳለ ፍጥረተ-ዓለም ማብቂያ የሌለው ዘልዓለማዊ ነው ይባላልን? ዛሬ ላይ ሳይንቲስቱ ከብዙ ውጣ ውረድ በኃላ በተፈነጠቀው የBig Bang ንድፈ ሀሳብ ፍንጭ ተማርከዋል:: የዚህን ወሰን የለሽ ፍጥረተ-ዓለም ዕጣ ፋንታ ምስረታና ጀማሬን ለማወቅ የBig Bang ንድፈ ሀሳብ ምቹ እድልን ፈጥሯል:: ለዓመታት ቆይቶ የነበረው የፍሬድ ሆሊ

" Static universe model" ውድቅ ሆኗዋል:: ከራሳቸው አንደበትም እያረጋገጡ ነው::ለአብነት ያክል ለብዙ ዘመናት ፍሬድ ሆሊን ደግፈው ሲከራከሩ የቆዩት ዴኒስ ሲማ የመጨረሻውን ውሳኔ መድረስ የቻሉት የBig Bang ንድፈ ሀሳብ በተሟላ መረጃ ጥናትና ምርምሩ ከተጠናቀቀ በኋላ መሆኑን ትዝታቸውን ያወሱናል::

*«በዚያ ወቅት " Static universe model" ደጋፊዎችና በንድፈ-ሀሳቡ ተመራማሪዎች መካከል የከረረና መራር ክርክር እንደነበር አስታውሳለሁ:: እኔ በወቅቱ አስተሳሰቡን ልክ እንደሆነ ለማሳየት የተወሰነ ሚና ነበረኝ:: ምክንያቱም በግዜው " Static universe model"ን እደግፍ ስለነበር ነው:: ነገር ግን እደግፍ የነበረውም እውነት*

*ይሆናል ቢዬ በንመተኩት አቅጣጫ ሳይሆን ንድፈ-ሀሳቡ በወቅቱ በለማረከኝ ነበር ለማለት እችላለሁ:: ሰር ፍሬድ ሆሊን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች የመሪነቱን ቦታ እንዲይዝ የቀረበውን መረጃ የመከላከል ሀላፊነት እንደተወጣሁ ትዝ ይለኛል:: በዚህ መልኩ በወቅቱ ወሳኝ ሚናዎችን ተጫውቼ ነበር::ነገር ግን መረጃዎቹ ጠንካራ መሰረት ስለነበራቸው ከበቂ በላይ መረጃ ውድድሩን በተሸናፊነት እንዲጠናቀቅ አድርጎታል:: ያኛ" Static universe model" ውድቅ ሆነ ማለት ነው::»*[8]

በማለት ሀሳባቸውን ሰንዝሯል:: ፕሮፌሰር ጂኦርጅ አቤል ከካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ የሰጡት አስተያየት ደግሞ:-

*«በአሁኑ ጊዜ ከበቂ በላይ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ፍጥረተ-ዓለም የተከሰተው ከቢሊዮን አመታት በፊት ሲሆን የመገኘቱም ምክንያት Big Bang ነው::» ፕሮፌሰሩ አክለው እንደገለፁት «ይሄንን ንድፈ ሀሳብ ከመቀበል ውጭ ሌላ ምርጫ የለም::» ብለዋል::*

አብይ ፈንዳታ ንድፈ-ሀሳብ ድል ከነሳ በኋላ መሰረቱ የቁሳዊ ፍልስፍና የሆነው" Static universe model" ውግዘት ገጥሞታል:: ከአብይ ፍንዳታው በኃላ ፍጥረተ-ዓለሙ እንዴትና በምን ሁኔታ ነበር? የትኛው ኃይል ነው ፍጥረተ-ዓለሙን እንዲገኝ ያደረገው? ይህ ትልቅ ፍንዳታ መቼ ነበር ያልነበረው? እነዚህ ጥያቄዎች አንድ ነገር ይጠቁማሉ::

በአርሁር ኢዲንግተን እንደተብራራው *«ለፍልስፍናው ዓለም የማይመች ነገር ቢኖር የፈጣሪ መኖር ነው:: በተለይም ለቁሳውያን::» ብለዋል::*

[8] Stephen Hawking, *A Brief History of Time: A Reader's Companion*, edited by Gene Stone, 1993, p. 63

በዚህ ዙሪያ ዝነኛው (atheist)[7] ፈላስፋ አንቶኒ ፍሊው የሰጠው አስተያየት ደግሞ፡-

«ለመጥፎ ነገር ተላቆ ንስሀ መግባት ለነፍስ መልካም ነው:: ስለዚህ ጅማሬውም ንስሀ ነው:: ብልሃተኞቹ አቴይስቶች(ኢ-አማኒያን) በጠፈረተኞቹ ተመራማሪዎች መካከል በተፈጠረው ስምምነት ሊያፍሩ ኢይገባም:: ምክንያቱም ተመራማሪዎቹ ቅዱስ ቶማስ በፍልስፍናው የላረጋገጠውን ለመለካከት ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ሰጥተውታል:: እርሱም ምንድነው ከተባለ? ፍጥረተ-ዓለም ጅማሬ አለው የሚል ነው:: ነገር ግን ከዚህ በፊት የነበረው የፍጥረተ-ዓለም ፍቺ ያለፍፃሜውም ሆነ ያለጅማሬው ፍጥረት ሊሆን ይህ ደግሞ ቀላል አረዳድና ግምት ሲሆን ተራ ግኝትም ነበር::ከዚህ መሰረተ-ሃሳብ የሚገኙ ማንኛውም እውነታዎች አማራጭ የሌላቸው መለኪያዎች አድርገንም እንቀበለው ነበር::እኔ እንደማምነው ይህ ውሳኔ ትክክል ነው እላለሁ::ነገር ግን አሁንም ቢሆን መታሰብ ያለበት ነገር ቢኖር ይሄንን ለመለካከት ከBig Bang ንድፈ ሀሳብ እውነታ አንጻር ታሪካዊ ንፅታውን መጠበቁና አቋም መያዙ ቀላልም አይደለም ምቹም አይሆንም» ብሎዋል::[8]

ብዙ ሳይንቲስቶች አቴይስቶችን በጭፍን አይከተሉም:: የኃያሉን ፈጣሪ ህልውና በፍጥረተ-ዓለሙ ሚናው ያረጋግጣሉ:: እርሱም ቁስ አካልና ጊዜን የፈጠረ ነው:: ከግዜና ከቁስ ጋር ጥገኛ ያልሆነ ራሱን የቻለ ነው:: ታዋቂው የስነ-ፈለክ ተመራማሪ ሀግሮስ እሄንን ጉዳይ አስመልክቶ ፡-

[7] በፈጣሪ መኖር የማያምን

[8]. Henry Margenau and Roy Abraham Varghese, eds., *Cosmos, Bios, Theos*, La Salle, IL.; Open Court Publishing, 1992, p. 241

*ጠለክ እንደ በታ የግዜ ፅንስ ሀሳብ ከፈጥረተ-ዓለም መፈጠር ጋር የተያያዘ ከሆነ፡- ለፍጥረተ-ዓለሙ መነሻ ምክንያቱ ፍጹም ጥገኛ ባልሆነው የግዜ ልኬት (ትይዩ-ግዜ) ከፍጥረት በኋላ ከሚታወቀው የግዜ ልኬት በፊት አንዳንድ ነገሮች ሂደቶችን አልፏል ማለት ነው። ይህ ውሳኔ ለፈጣሪ ያለንን አመለካከት እንድናስተካክል እጅግ አስፈላጊ ነው። በዚህ አማካኝነት ፈጣሪ ምን እንደሆነና ምን እንዳልሆነ ይጠቁመናል። ስለዚህ የፍጥረተ-ዓለሙ ፈጣሪ እንዳልሆነና በአንጻሩ ደግሞ ፈጣሪ የፍጥረተ-ዓለሙ አካልና አባል እንዳልሆነ ያመላክታል»* *

የግዜ የቦታና የቁስ አካል ፅንሰ-ሀሳብ የመጣውም ከፍጥረተ-ዓለም ከ(universe) ምስረታ በኋላ ነው። እነዚህን ነገሮች ካለመኖር ወደ መኖር ያስገኘው ልዕለ ኃያሉ ፈጣሪ ነው። እርሱም ጊዜን ቦታንና ቁስ አካልን አስገኘ። እንጂ አያስገኙትም። እርሱ ያካበባቸዋል እንጂ አያካብቡትም። ሕልውናቸውም በፈጣሪ ላይ ሲሆን የርሱ ሕልውና ከነርሱ ነፃና ገለልተኛ በራሱ የተብቃቃና ራሱን የቻለ ባጠቃላይ በነርሱ ላይ ጥገኛ ያልሆነ ነው።

## በጠፈር ውስጥ የሚስተዋለው ረቂቅ የሆነ ሚዛናዊ ስርዓት

በእውነቱ ከሆነ የBing Bang ንድፈ-ሀሳብ ከቁሳዊያን ይልቅ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በአቴይስት ፈላስፎች ላይ ያስደረው የስነ ልቦና ተፅዕኖ ንስሀ እንዲገቡ እንዳስገደዳቸው አንቶኒ ፍሊውን ለማየት ችለናል። በንድፈ-ሀሳቡ መሰረት ፍጥረተ-ዓለም ካለምንም ነገር መፈጠሩን ብቻ ሳይሆን እጅግ በረቀቀና በተቀነባበረ ፕላን መሰረት የተገነባ መሆንን ይተነትናል። Big Bang የተካሄደውም ከአንዲት መነሻ ነጥብ በተፈጠረ ወሰን የለሽ ፍንዳታ ሲሆን በውስጡም የፍጥረተ-ዓለሙን ቁስና ሀይልን አካቶ የያዘ ሲሆን፡- በጠፈር ውስጥ እጅግ በሚያስፈራና መጠኑ ይህ ነው ከማይባል

---

* . Hugh Ross, Ph.D., *The Creator and the Cosmos*, Navpress, 1995, p. 76

ፍጥነት ወደ ሁሉም አቅጣጫ መበታተኑን ሲያብራሩ፡- ከነዚሁ የቁስ አካልና የኃይል ፍንጥቅጣቂዎች መካከል እጅግ አስገራሚና ኃያል መመጣጠን ወይም ሚዛን ተከስቶዋል፡፡

ከነዚህ ውስጥ የከዋክብት ክምችቶች ( Galaxies)፤ ከዋክብት፤ ፀሀይና በዙሪያዋ የሚገኙ መሬትን ጨምሮ ፕላኔቶችን ፤የጠፈር አካላትን ያካተተ ሥርዓተ-ሚዛን ተፈጠረ፡፡ በሌላ አባባል «የፊዚክስ ሕጎች» ብለን የምንጠራቸው ስርዓቶች ሲሆኑ በመላው ዓለም የማይለወጥና አንድ ወጥ ቋሚ መስፈርት ወይም የመለኪያ አሀድ ማለት ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለውም ከአብይ ፍንዳታው በኋላ በተቀነባበረ ሚዛን ነው፡፡ ምክንያቱም ፈንዳታው ይህንን ረቂቅ የሆነ ሚዛን ወይም አንፃራዊ ግፊት ማምጣት አይችልም፡፡ በእውኑ ዓለም የምናያቸው ብዙ ፍንዳታዎች ሲንዱ ሲያጠፉና ሲያወድሙ ነው የምንመለከተው፡፡ ለአብነት የከል የአቶምና የሐይድሮጂን ቦንብ ፍንዳታዎችን፣ ለደድ እሳት፤ የዕሳተ-ገሞራ ፍንዳታ፤ የስርዓተ-ፀሀይ ፍንዳታዎችን ያየን እንደሆን ውድመታቸው የከፋና የትዩለሴ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ ስለዚህ ከተፈጥሮ ባህሪ ውጭ የሆነ አንድ መለኮታዊ ሀይል (Super natural) ከፍንዳታው በስተጀርባ መኖሩን ያሳያል፡፡ እነዚህ የጠፈር ብትንታኝ አካላት ኋላ ላይ በተፈጠረ መያያዝ ወይም ሚዛን ስርዓት-ያሳያዘ አካል መኖር አለበት፡፡ እርሱም «ፈጣሪ» ነው፡፡ ይሄንን ጥያቄ የኋላኋላ ስህተታቸውን አምነው የተቀበሉና ለአብይ ፍንዳታ ንድፈ ሀሳብ ተቀናቃኝ ሆነው የቆዩት ሰር ፍሬድ ሆሊ በደንብ ሲያብራሩት፡-

*«Big Bang ፍንዳታ ከአንዲት ነጠላ ነጥብ ፍንዳታ መነሳቱን ሲያትት ነገር ግን ፍንዳታ ቁስ-አካል እርስበርሱ እንዲበታተን ያደርጋል፡፡ Big Bang በኋላ ላይ ምስጥራዊ በሆነ ሁኔታ አንፃራዊ የርስ በርስ ትስስር/የመገፋፋት ሀይል / በአንድ ቦታ ሊረጋ ችሎዋል፡፡»* [10] ብለዋል፡፡

ሰር ፍሬድ ሆሊ እያደይዘው ሲናገሩ የBig Bang አስገራሚና ወጣ ያለው ገፅታ «ምቹ የመኖሪያ ዓለም» መገኘቱ ነው፡፡ ይህ ሕይወት የሚኖርበት ምቹ ፕላኔት ሁኔታ እጅግ ውስብስብ በጭራሽ ሊሆን የማይችል እንደው በአጋጣሚ ተከሰተ ብሎ ለመናገር የማይሆን አስተሳሰብ ነው ይላሉ፡፡ በዚህ ዙሪያ ፕሮፌሰር ፓውል ዳቪስ የተባሉ ዝነኛ (theoretical physist) እንደገለጹት« *ከፍንዳታው ሊገመት*

[10]. W.R. Bird, *The Origin of Species Revisited* . Nashville: Thomas Nelson, 1991: originally published by Philosophical Library in 1987, p. 462

የማይቻል ረቂቅ መገፋፋት በተመጣጠነና ወጥ በሆነ ሁኔታ እንዴት እየሰፉ መሄዱን ቀጠለ?» የሚገርምና ተአምር መሆኑን ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ችለዋል:: እንደ ፕሮፌሰሩ አገላለፅ

> «ከአብይ ፍንዳታ በኃላ ፍጥረተ-ዓለም የመለጠጥ ፍጥነቱ ቅንጣት ታክል ለውጥ ቢያሳይ፡- ሌላው ቀርቶ የአንድ አንድ ቢሊዮንኛ (1/1000 000 000) ለአንድ እንኳን ልዩነት ቢያመጣ፡- አንድም በፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ የሚኖር ኮከብ እንኳ ባልተመሰረተ ነበር» ይላሉ:: «እጅግ በጣም ረቂቅ በጥንቃቄ የተሞላ ልኬት መሰረት የተመሳው ፍጥረተ-ዓለም መዘርጋት መሰረታዊውን ሕልውና በሚጠብቅ መልኩ ራሱን ጠብቆ ፍጥረተ-ዓለሙ ለዝንተ-ዓለም እየተለጠጠ ይኖራል:: ከተለመደው ፍጥነት ለትዕቢት ቢዘገይ ሙሉ ለሙሉ በዚያች ቅፅበት እንዳለ ይወድማል ወይም (collaps) ያደርጋል:: በአንጻሩ ደግሞ ጥቂት ቢፈጥን ፍጥረተ-ዓለሙ የጠፈር አካላትን ጨምሮ ዳግም ላይመለሱና ላይገናኙ ሙሉ ለሙሉ ይበታተኑ ነበር:: በሁሉም ሰው ሕሊና ስለዚህ ጥንቃቄ የተሞላበት ረቂቅ የሆነ መሳሳብ አለያም የርስበርስ እንዝራዊ መገፋፋት:: የፍጥረተ-ዓለሙን የመስፋፋት ፍጥነት ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ተጠብቆ መኖሩ እንዲችል ያደረገው መለኮታዊ ሀይል መኖሩን ያመላክታል:: በሁለቱ ምክንያቶች መካከል ያለው ቀጭን መስመር ላይ ለመውደቅ ድንገተኛ መቅሰፍት ቢያጋጥመው በአንድ ሰከንድ ጊዜ ውስጥ ኃይም ቀደም ከነበረው የመለጠጥ ገድፍ የፀና መሰረት ባይኖረው ኖሮ በእርግጠኛነት የመዘርጠጥ ፍጥነቱ 10-18 እጥፍ የሚያክል ልዩነት ያመጣ ነበር::ይሄው ልዩነት በመካከሉ የተፈጠረውን ረቂቅ መመጣጠን ለማዛባት በቂ ናት::የፍጥረተ-ዓለሙ የመፈንዳት ብርታት ሙሉ ለሙሉ በማይታመን ሁኔታ

*በትክክለኛ የሰበት ሀይል የተመጠነ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ ሚዛናዊ ሁብር የተፈጠረው በአርጌው ወይም በድሮው Big Bang ነው:: ነገር ግን ይህ ሊሆን የቻለው በፍንዳታው አማካኝነት የተፈጠረ አይደለም:: ነገር ግን አድግ በረቀቀና ግበባዊ በሆነ ሁኔታ የተሰላ ሚዛን ስለሆነ ነው::»*[11]

የፊዚክስ/የተፈጥሮ ሕጎጋቶችም አብረው ከ Big Bang ንድፍ ሀሳብ ተያይዘው ሊከሰቱ ችለዋል:: ይህ የፊዚክስ ሕግ ላለፉት 15 ቢሊዮን አመታት አንድም ሳይለወጡ ኖሮዋል ወደፊትም ሳይለወጡ ይኖራሉ::ይሄንን የፍጥረተ-ዓለም ሕገ-ሚዛን (Equilbrum) ከ1400 አመት በፊት በቁርአን እንደሚከተለው ተጠቅሶዋል:-

«ሰማይንም ከፋ አድርጎ አጸናት:: በላይዋም ሚዛኑን አስቀመጠ:: ሚዛን ላይ አትበድሉ በትክክል መዝኑ ሚዛንን አታጉድሉም::» (ቁርአን 55:78)

## የቁስ አካል /አተም አፈጣጠር

አተምን ጨምሮ ለግንባታ ግልጋሉት የምናውለው ቁሳቁስ የተገኘ ው ከአብይ ፍንዳታ ወይም ከBig Bang በኃላ ነው:: እነዚህ አተሞች በአንድነት መላውን ፍትረተ-ዓለም ጨምሮ ውስጣዊ ስርዓቱን ማለትም ከዋክብቱን፤ መሬትን፤ ስርዓተ-ፀሀይን ጨምሮ የተሰሩት ከዚሁ ቁስ ወይም አተም ነው::አተም በፕላኔታችን መሬት ላይ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ምስረታ ግብአት ሆነዋል:: በዙሪያችን የምንመለከተው ነገር በሙሉ:: መላ አካላችን ጨምሮ የተቀመጡበት ወንበር፤ አሁን እያነበቡት ያለው መፅሀፍ፤ ከቤትዎ መስኮት አሻግረው የምያዩት ሰፊ የተንጣለለው

[11] . W.R. Bird, *The Origin of Species Revisited* , Nashville: Thomas Nelson, 1991; originally published by Philosophical Library in 1987, pp. 405-406

ህዋ ፣የምንረገጠው አፈር፣ የምንመገባቸው ፈራፍሬዎቹ ፣እፅዋቶቹ ሁሉም ባጠቃላይ የዚሁ ቁስ አካል (አተም) ግንባታ ውጤት ነው፡፡

ታዲያ አተም ምንድን ነው? እንዴት ለሁሉም ነገር ግንባታ መሰረት ሆነ? ምን አይነት አወቃቀር አለው? የአተምን መዋቅር ስንመረምረው እጅግ ወጣ ያለ ልዩ ንድፍና ስርዓት እንዳለው እንመለከታለን፡፡ ማንኛ ውም አተም መዕከላዊ ክፍል ወይም (nucleus) የአቶም እንብርት ሲኖረው፡- በዙሪያው ፕሮቶንና ኒውትሮን አብሮት አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአቶሙን እምብርት ወጥ በሆነ ፍጥነት በምህዋራቸው በዙሪያው የሚሽከረከሩ ኤሊክትሮኖች አሉ፡፡ እነዚህ ኤሌክትሮኖች በአማካይ ፍጥነት በአንዲት ነጠላ ሰከንድ 1000 ኪሎ ሜትር ይሽከረከራሉ፡፡ በአንድ አቶም ውስጥ ያሉት የፕሮቶንና የኤሌክትሮን መጠን እኩል ናቸው፡፡ ለዚህ ምክንያቱም ሁለት ተቃራኒ ፅንፎች ማለትም የፕሮቶን ፖዘቲቭ ቻርጅና የኤሊክትሮን ኔጌቲቭ ቻርጅ ሁሌም እኩል መጠን ስለሚኖራቸው ነው፡፡

ከሁለቱ አንዱ ልዩነት ቢያመጣ አተም የሚባል ነገር አይኖርም፡፡ በመካከላቸው ያለው ኤሊክትሪካዊ ስበት መጠን (electro magnetic balance) ይዘባል፡፡ በአቶም ዕምብርት (nuclues) ዙሪያ ያሉት የፕሮቶን የኒውትሮንና የኤሊክትሮን ሞሉኪውሎች የተረጋጉ አይደለሉም፡፡ ሁሉም በምህዋራቸው አንዱ የሌላውን መስመር ሳያዛባ በአተሙ ዙሪያ ይራወጣሉ፡፡ ይህ ፍጥነት አንዱ ከአንዱ የሚመጥን ነው፡፡

ስለዚህ ለአተም መኖር ትልቅ ነገር ያበረክታል፡፡ በዚህ ምክንያትም ምንም ስርዓት አይዛባም፡፡ ለውጡ ሳይዛባ ተጠብቆ ይኖራል፡፡ ይህ ትዕይንት በከፍተኛ ስርዓትና ቅደም ተከተል የተቀነባበረና ምንም ነገር በሌለበት ነገራቶችም ሊገኙ የቻሉበት ከታላቁ አብይ ፍንዳታ በኋላ ነው፡፡ እንደውም Big Bang ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ያለ ፕሮግራም በአጋጣሚ

የተፈጠረ ፍንዳታ ቢሆን ኑሮ፡- የሚከተለው ቀውስና ደመነፍሳዊ ክስተት ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ተባታትኖ በቀረ ነበር። በርግጥ እንከን የለሽ ስርዓት ከፍጥረተ-ዓለሙ ጀማሬ በኋላ በየ ቦታው ተደንግጓል። ለእብነት ያህል አተሞች የተሰሩትም በተለያየ ግዜና ቦታ ነው።

ነገር ግን እጅግ በጣም የተደራጁ ከመሆኑ እንጻር በአንድ ፋብሪካ የተመረቱ ይመስላሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ኤሌክትሮኖች ኒውክለሱን ካገኙ በኋላ በዙሪያው ይሽከረከራሉ። ከዚያ በኋላ አተሞች እርስ በርስ ተገናኝተው ቁስ አካል ይገነባሉ። ታዲያ የእነዚህ ሁሉ ቅንጅት ውጤት፡- በዓለማችን ላይ በገሀድ የምንመለከተውን ውስብስብ መዋቀርና ትዕይንት እንዲመሰርቱ አስችሏል። ስለዚህ ይህ ውስብስብ ነገር ሁሉ ትርጉምና አላማ ያለቸውና ምክንያታዊ ነገሮች መሆናቸውን መረዳት ያሻል። በዚህ ፍጥረተ-ዓለም አላስፈላጊ ጥቅም የለሽና አለማ የለሽ የሚባል አንድም ነገር የለም። እያንዳንዱ ረቂት ደቂቅ አሀድም ሆነ ግዙፍ አወቃቀር ያለው ነገር በሙሉ በርፈ ብዙ አለማ ያለው ነው።

እነዚህ ገሀዳዊ እውነታዎችና መረጃዎች የፈጣሪ መኖር ልዩ ምልክቶቹ ናቸው። እርሱም የሁሉም ነገር ባለቤት ነው። እያንዳንዱ ነገር የተገኘውም በርሱ ፍላጎትና ፍቃድ ነው። ከርሱ ቁጥጥርና እዝ ውጭ አንድም ነገር የለም። በቁርአን ውስጥ ፈጣሪ ስለፍጥረታቱ ሲያወሳ እንዲህ ይላል።

«እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በእውነት የፈጠረ ነው። እንዲሆን የሻውን ነገር «ሁን» የሚልበትንና ያም ነገር ወዲያውኑ የሚሆንበትን ቀን አስታውስ ቃሉ እውነት ነው።» (ቁርአን 6 : 73)

## ከ Big Bang በኋላ

*«በእርግጥ አንድ የማይካድ እውነታ አለ። እርሱም ፍጥረተ-ዓለሙ ዓላማና ግብ እንዳለው አሙን መሆን ነው። በአጋጣሚ አሊያም በእድል የተገኘ አይደለም። አንድዳንድ የቆኝ ሰዎች አመለካከት*

*ፍጥረተ-ዓለም ድሮም ነበረ ወደፊትም ይኖራል:: የሚል አስተያየት ሊኖራቸው ይችላል:: ይህ ተራና ከንቱ አመለካከት ነው:: እኛ ነታችንም በዚህ ፍጥረተ-ዓለም ላይ ድንገተኞች ነን ብለን እናስባለን:: እንደዚህ አይነት የተዛባ አመለካከት አሁን ባለንበት ፍጥረተ-ዓለም ትክክለኛና ቀናኢ አመለካከት እንዲኖረን አይረዳንም:: እኔ እንደማስበው ፍጥረተ-ዓለም አሁን ከተሰጠው ስያሜ በተለየ መልኩ ጥልቅና የሰፋ ነገር ነው:: ስለ አፈጣጠሩ እንኳ ቢሆን ቅንጣት ታክል ፍንጭ ነው ያለን:: ስለዚህ ፍጥረተ-ዓለሙ እንደስፋቱ የሰፋ ዓለማ ያለው ነው::»[13]*

ከላይ ያየነውን ሀሳብ የሰጡት ሮጀር ፔንሮስ ጥሩ የአመለካከትና የግንዛቤ ማዕድ ጠቁመውናል:: በሌላ አበባላቸው ብዙ ሰዎች ስለፍጥረተ-ዓለም ያላቸው የተሳሳተ ግንዛቤን ለመጠቆም ፈልገው ነው:: እንከን የለሽ አፈጣጠሩንና ካለምንም መገኘቱን በተሳሳተ መልኩ ተረድተውት እነርሱ ግን ያለምንም እፍረት አለማና ምክንያት ሳይኖራቸው በፍጥረተ-ዓለሙ ላይ የፍጥረታት አንዱ አባል መሆናቸውን ዘንግተው በከንቱ ፍልስፍና ይኖራሉ:: ነገር ግን እንዴት ፍጥረተ-ዓለሙን እንደዚህ ተራ አድርገን እናስበዋለን? በርግጥ ዛሬ ላይ ይሄንን እንከን የለሽ አስገራሚ ስርዓት ሊመሰረት የቻለው? ከ Big Bang ፍንዳታ በኃላ ነው::

ይሄንን ቁርጠኛዊ እውነታ የሳይንስ ማህበረሰብ ለፍጥረተ-ዓለሙ መፈጠር መንስኤ ሆኗል በማለት አፅድቀዋል::ይህ ወደረ የለሽና አስደማሚ ፕላንና ስርዓት ፍጥረተ-ዓለም የተገኘው በመለኮታዊ ኃይል መሆኑን ይጠቁማል:: ፈጣሪም በእውቀቱ ወሰን የለሽ ኃያልና ጥበበኛ ሲሆን እርሱም ቁስ አካልን ካለምንም ያኖረ ነው:: እርሱም በፍጥረታቱ ላይ ዘውታሪ፤ ተቆጣጣሪና፤ አስተናባሪና አስተዳዳሪ ነው:: ፈጣሪ አምላክ

---

[13] . Stephen Hawking, *A Brief History of Time: A Reader's Companion*, edited by Gene Stone, 1993, p. 142

የሰማያትና የምድር ገኘር በመካከላቸውም ሆነ በውስጣቸው ያለውን በሙሉ የሚያስተዳድር ነው።

ይህ ሁሉ መረጃ የሚያሳየን በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገኖ የነበረው የቁሳዊ ፍልስፍና ቀንና በ21ኛው ክፍለ ዘመን የተደረገው ሳይንሳዊ የጥናትና የምርምር ውድቅ መሆኑን ያስገነዝበናል። አንድ ቀን ደግሞ ቁሳዊ ፍልስፍና ታሪክ ሆኖ ኋላ ቀርና ከንቱ እምነት በማራመድ ሳይንስንና እማከንዮን በመጻረር የብዙ ህዝብ አመለካከትን ያዛባ ታሪካዊ ውግዘት የሚደርስበት ቀን በርግጥ ሩቅ አይደለም።ምክንያቱም የሰብአዊውን ፍጡር ለፍጥረተ-ዓለሙ የተከላሸ አመለካከት እንዲኖረውና ለአምላክ ተገዥነና ህግጋቱንም ገቢራዊ እንዳያደርጉ ግብታዊና ቁሳዊ ፍጥረት እንዲሆኑ ተጽዕኖ ስር አሳድሮዋል።

## በሰማይና በመሬት ላይ የሚስተዋሉ ምልክቶች

እንበልና እርስዎ የአንድ ትልቅ ከተማ በውስጡ ካለው በሚሊዮን የሚቆጠር ህልቆ መሳፍርቱን ጨምረው አቋቋሙ ይባል። በዚያ በቋቋሙት ከተማ ውስጥ ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች፣ መንታ መንገዶች፣ የባቡር ሃዲዶችና ጣቢያዎች፣ የአየር ማረፊያዎች፣ ትላልቅ የገበያ አዳራሾች፣ አውራጎዳናዎች ፣ወንዞች፣ ሀይቆች ፣ደኖችና ሌሎችም በርከታ ነገሮች ሲኖሩ በከተማው ውስጥ የሚኖርው በሺዎች የሚቆጠር ህዝብ በአውራ ጎዳናዎች ተንቋለዋል። በየቤቱም ሆነ በየመስሪያ ቤት ያለው ሕልቆ መሳፍርት ህዝብ ጨምሮ ሁሉንም በዝርዝር ግምት ውስጥ ከተው። ለላው ቀርቶ የትራፊክ መብራቶች ፖስታ ቤቶች የማስታወቂያ ሰሌዳዎ የአውቶብስ ፌርማታዎችንም ሳይቀሩ ግምት ውስጥ ከተቷቸው።

*ታዲያ አንዱ ለከተማው እንግዳ ግለሰብ ወደርሶ ይጠጋና «ይህ የምታዩት ከተማና በውስጡ የሰፈረው ህልቆ መሳፍርት በሙሉ*

የተመሰረተው አንድ ትልቅ ገደል በፈጠረው ፍንዳታ ፍንጥርጣሪ ነው።።ቢሉዎት የማሰሰቡን የአእምሮ ሁኔታ በትዕበት ማሰብ አይጀምሩምን? እርሶ ግን ስለከተማው ፕላን ዝርዝር መረጃ የውቃሉ። እያዳንዱን ነገር በጥንቃቄና በከፍተኛ ውድ መስዕዋት ያቋቋሚት ከተማ ናት። እንበልና የከተማዋን መሰረት ሙሉ ለሙሉ አስተካክከለው ቢጨርሱና በፕላኑ መሰረት ከሚሰፍረው ሕልቆ መስፈርት አንድ ነጠላ ነገር ቢረሱ አሊያም ቦታ ቢያቀያይሩ እቺው ስህተቶ በመሰረቱት ከተማ ላይ ምቹ ስርዓትና ሚዛን ላይ እንከን ፈጥሮቦዎት አያስተውሉምን ?

እኛም እየኖርን ያለንበት ዓለም በዚህ መልኩ ይሄንን ሁሉ ህልቆ መሳፍርት አካቶ ያቀፈ ነው። ከነዚህ አባላት የአንዱ አለመኖር በመሬት ላይ የህይወት ግብአተ መሬቷ ሊፈፀም እንደሚችል ያምናሉን? ጠቅላላ የፍጥረተ-ዓለሙ ስርዓት ሊወድም ። እንደሚችል ያውቃሉን? እያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳይ ከትንሹ የቁስ አካል መሰረት ከሆነው አተም እንስቶ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ጋላክሲዎች፣ የከዋክብት ክምችቶች፣ ጨረቃ፣ ስርዓተ-ፀሀይ በሙሉ ባማረ ሁኔታና ትስስር ስራቸውን በቅንጅት እውን እያደረጉ መሆናቸው ተረድቷልን? አዎ! ይህ በደንብ የተደራጀ ወደርና እንከን የለሽ ስርዓት በገሀድ እንደምንመለከተው አላማውን ሳይስት ሀላፊነቱን ይወጣል።

ይህ ለቢሊዩን አመታት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ስርዓት ያለሚቋረጥ ተግባሩን እንደሚወጣ እርግጠኞች ነን። ስለዚህ ሰዎች ያለስጋት በነፃነት ለብዙ ዓመታት የሚሆን እቅዳቸውን ይነድፋሉ። ማንም ግለሰብ ፀሀይ በሚቀጥለው ቀን ልትጠፋ ትችላለች ብሎ አይጨነቅም።አብዛኛው ሰው መሬት በፀሀይ የስበት ሀይል የመሰበር እድል ያጋጥማትና ከዚያም ወደ አንድ ያልታወቀ ጨለማ ቦታ ልትወረወር ትችላለች አሊያም እርሷን ከሚመጥን ግዙፍ ፕላኔት ትላተማለች ወይም ከዚህ መቅሰፍት ማነው የሚታደጋት? ብሎ አያስብም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ሰዎች ለመተኛት ሲፈልጉ በከፍተኛ መተማመን ነው:: የአተነፋፈስ ስርዓታቸውም ሆነ የልቦቻቸው ምት ልክ እእምሮዋቸው እንደሚያሸልበው ያሸልባል የሚል ስጋት አይፈጠርባቸውም ። ነገር ግን ከሁለቱ አንዱ ጥቂት ለማይባል ሰኮንዶች ስራውን ቢያቆም የህይወታችን ወሳኝ ስርዓት ምን አይነት አደጋ እንደሚገጥመው እሙን ነው:: በየ ጥጋጥጉ ዓይናችንን ከፍተን የምናየው ትዕይንት ሁሉ የምናይበት አይናችንን ጨምሮ የሰራ መላ አካላታችን የሚገዛ አንድ ሀይል ከበስተጀርባቸው እንደሚቆጣጠረው፣ እንደፈጠረውና እርስ በርስ ያስተሳሰረው መሆኑን ይመሰክራሉ:: እርሱም እያንዳንዱን ዝርዝር ነገር ካለመኖር ወደ መኖር -ያመጣው ነው::በተከበረው መለኮታዊ ቃሉም እንዲህ ይለናል:-

« ያ ሰባቱን ሰማያት አንዱን ከሌላው በላይ አድርጎ የፈጠረ (አምላክ) ነው:: በአል-ረህማን [10]ፈጠራ ውስጥ ቅንጣት ጉድለትን አትመለከትም:: (የሰማያትን አፈጣጠር) በሚገባ አስተውል፤ እንዳች ስንጥቅን (ጉድለትን ታያለህን?» ደግመህ ደጋግመህ አስተውል! ዓይንህ የተዋረደና የደከመ ሆኖ (እንዳች ጉድለት ማየት ተስኖት ወደ አንተ ይመለሳል» ቁርአን 67:3-4)

በመሬትና በጠፈር ላይ የሚስተዋለው ክስተት በሙሉ ስለፈጣሪው አፍ አውጥቶ ይመሰክራል:: የፈጣሪን ልዩ ምልክቶችን ዘርዝረን እንጨፋቸው ብንል አያሌ የኢንሳ ይክሎፒዲያ ጥራዞች አይበቁንም:: እነዚህ ገሀዳዊ ሀቆች ትንሽ ቆም ብለን እንድናስብ ያሚያደርጉን መሆናቸውን ስንቶቻችን ነቅተናል?

10 «አል-ረህማን» ከአላህ መልካም ስሞች መካከል አንዱ ሲሆን ትርጉሙም እጅግ በጣም ሩህ ሩህና አዛኝ ማለት ነው::

# ሳይንቲስቶች የፈጣሪን መኖር ፍንጭ እያረጋገጡ ነው

እስከሁን ለማየት የሞከርናቸው የፍጥረተ-ዓለሙ ጋሀዳዊና ሳይንሳዊ እውነታዎችና ባህሪት የፈጣሪን የመኖር ሕልውና ያፀድቃሉ፡፡በሳይንስ የተረጋገጡ አንዳንድ ማጠቃለያዎች ፍጥረተ-ዓለም ፈጣሪ እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ፈጣሪም እንከን የለሽ ኃያል ጥበበኛና አዋቂ ነው፡፡ ፈጣሪን ለማወቅ ሀይማኖት ያመላክተናል፡፡ ስለዚህ በቀላሉ ሳይንስ ሀይማኖታዊ ድንጋጌዎችን ለመመርመር ምርጥ ዘዴ ነው፡፡ ነገር ግን ዘሬ ላይ አንዳንድ ሳይንቲስቶች በሳይንስ ስም ሁሉቱን ነጦለው በአንድ አቋም በመጽናት መሰረቱን ንደዋል፡፡ እንደነርሱ አመለካከትም ሳይንሳዊ እውነታዎች የፍጥረትን እውነታ ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም ይላሉ፡፡

ይህ አቋምም ቀደም ብሎ የነበረው አቴይስታዊ ግንዛቤ የፈጠረው ጠባሳ ሲሆን፦ በሳይንሳዊ ማረጋገጫ ዘዴና ዳታ ግብአት አምሳክን ማግኘ ት የማይቻል ነገር ነው ይላሉ፡፡ እንደነርሱ አቤቱታ ሳይንስና ሀይማኖት ሁለት የማይስማሙ ፅንፈኛ አቋሞች ናቸው ይላሉ፡፡

ነገሩን ልብ ብለን ስናየው የአቴይስቶቹ ሳይንሳዊ ግንዛቤ የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው፡፡ ከጥቂት ዘመናት በፊት ሳይንስና ሀይማኖት እርስበርሳቸው የማይጣረሱ ነበሩ፡፡ ሳይንሳዊ እውነታዎችም የፈጣሪን መኖር ማረጋገጫ መንዶችም ነበሩ፡፡ ከግዜ በኋላ የተከሰተው የአቴይስቶች ግንዛቤ መሰረት ያደረገው የቁሳዊነትና የግብታዊነት (positivist) ፍልስፍና በ18ኛውና በ19ኛው መቶ ክፍለዘመን የተጋረጠ መጤ አመለካከት ነው፡፡ በተለይ የስነ-ቅሪት ተመራማሪ የነበረው ቻርልስ ዳርዊን በ1859 ከረቀቀው የስነ-ዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ (Theory of Evolution) በኋላ ነው፡፡ የቁሳዊ ፍልስፍና ሪዕዮተ-ዓለማዊ መሰረቱን የያዘው ከዚህ ንድፈ-ሀሳብ ነው፡፡ ሀይማኖታዊ ትንታኔዎችን ወደጎን በመተው ንድፈ-ሀሳቡን አማራጭ አድርገው ያዙ፡፡

እንደ ስነ-ዝግመተ ለውጥ ንድፍ ሀሳብ መሰረት ፍጥረተ-ዓለም ባጋጣሚ የተከሰተ እንጂ ፈጣሪ የሚባል ነገር የሌለው ነው አሉ። ከዚህች አቋም ጋር በተያየዘ ብዙ ቢወዛገቡም የኋላ ኋላ ሀይማኖት ከሳይንስ ጋር የሚጣረስ የእውቀት ሳንክሳር ነው ብለው ፈረጁት። ለአብነት ያህል ብሪታኒያውያኑ አጥኚዎች ሚካኤል ቤጀንት፣ ሪቻርድ ሌህ እና ሄንሪ ሊንከን በጉዳዩ ላይ እንዲህ በማለት ፅፈዋል፡-

*«አይዛክ ኒውተን ከነበረበት አንድና ግማሽ ክፍለ ዘመን በኋላ እሲያም ከቻርለስ ዳርዊን ግማሽ ምዕተ-ዓመት በፊት ሳይንስ ከሀይማኖት ተለይቶ አይታይም ነበር። የጎላ ቁርኝትም ነበረው።ከሳይንስ ጋር ከፍተኛ ክብር ይሰጠውም ነበር። ነገር ግን በዳርዊን ጊዜ የነበረው ሳይንስ ሀይማኖት ለዘመናት ፍፁማዊ መለኮታዊ ራዕይ መሆኑ ተዘንግቶ ከሰንጠረዥ እንዲወጣና ከሳይንስ ጋር እንዲፋታ ተበይኖበታል። ከዚያ በፊት እንደሚታወቀው መለኮታዊው ሕግ ለሁሉም ምንጭና የጸና መሰረትም ነበረው።ይህ መሆኑ ቀረና የኋላ ኋላ የዳርዊን ግዜ ሳይንስና ሀይማኖት እንዳይጣጣሙ አድርገው አጣረሱ።ከዚያ በኋላ ሳይንስና ሀይማኖት አብረው ሊጓዙ አልቻሉም። ብዙም ሳይቆይ እርስ በርስ አቃረኗቸው። የሰው ልጅም ከሁለት አንዱን ለመምረጥ ተገደደ።»*
ብለዋል።

ከላይ እንዳየነው በሁለቱ መካከል የመለያየት አደጋ አባዜው ርዕዮተ-ዓለማዊ ሆነ።አንድዳንድ ሳይንቲስቶች በቁሳዊ ፍልስፍና ፅኑ እምነት ነበራቸው። እነርሱም ፍጥረተ-ዓለም ፈጣሪ የለውም ለማለትና ከዚህ ፅንሰ-ሀሳብ የተለያዩ ንድፍ ሀሳቦችን ለመንደፍ ተገደዱ።በተለይም የስነ-ዝግመተ-ለውጥ (Evolution theory) እጅግ በጣም አስፈላጊ ግብአት ሆኗቸዋል። በስነ-ከዋክብት ጥናት የተወሰኑ ፅንሰ-ሀሳቦች ሊመሰርቱ ችለዋል። «steady state theory» በመባል ይታወቃል።

ነገር ግን እነዚህ በሙሉ የፈጣሪን ህልውና የማይቀበሉ ነበሩ፡፡ ከሳለፍናቸው ትምህርቶች እንደተመለከትነው፡- ሳይንስን የተፃረረ መሆኑ ተደርሶበታል፡፡

ዛሬም ቢሆን አንዳንዶች ፅንስ ሀሳቡን የሙጥኝ በማለት ሁሉንም ሳለመቀበል የሚያደርጉት ወግ አጥባቂነትና ግብታዊነት ይስተዋላል፡፡ ይህ ሁሉ በፈጣሪ ላይ ላለማመን የሚደረግ አዝማሚያ ነው፡፡ ታዋቂው የእንግሊዝ የስነ-እንስሳትና የአዝጋሚ ለውጥ ተመራማሪ D.M.S. ዋትሶን እርሱና መሰል ጓደኞቹ የዝግመተ ለውጥ ቀነኛ አቀንቃኝ የሆኑበት ምክኒያት ሲያብራራ

*«ነገሩ የዝግመተ-ለውጥ ንድፍ ሀሳብ በቀጥታ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በሉጂክ የተደገፈ ጠንካራ መረጃ ያለው እውነታ ነው ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ለዚህ ግልፅ ተአምርና ልዩ ፍጥረት ብቸኛው አማራጭ ስለሆነ ነው፡፡»*[14]ብለዋል፡፡

እንደ ዋስቶን አባባል« ልዩ ፍጥረት» ማለት የአምላክ ፍጥረት ነው፡፡ እነዚህ ሳይንቲስቶች እውቅና እንደሰጡት ከሆነ «የማይቀበል» ነገር ብለው ሲደመድሙ በርግጥ ሳይንሳዊ መረጃ አለውን? ያለጥርጥር አይደለም ቀደም ብሎ የነበረው ሳይንስ የፍጥረትን እውነት ያረጋግጣል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ዋስቶን ይሄንን ጋሀዳዊ እውነታ ያልተቀበለበት ምክንያት የፈጣሪን የመኖር ጥያቄ ሳለመቀበል ነው፡፡ ውሳኔው ከርሱም ውጭ ባሉ የዝገመተ-ለውጥ ንድፈ-ሀሳብ አቀንቃኞች ተመሳሳይ ነው፡፡ የዚህ ንድፈ-ሀሳብ አራማጆች በርግጥም በሳይንስ ስም ቁማር ተጫውተዋል፡፡ ለምን ቢሉ ለቁሳዊ ፍልስፍና አሳማቸው ሳይንሳዊ አስመስለው ቀለም ቀብተው አጣመው አቅርበዋል፡፡

[14]. D.M.S. Watson, "Adaptation", *Nature*, no. 124, p. 233

በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የጄኔቲክስና የዝግመታዊ ለውጥ ንድፍ ሀሳብ ተመራማሪ የሆኑት ሪቻርድ ሊዎንቲን በዚህ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን ሲሰነዝሩ፡-

*«ይህ ጉዳይ በሳይንሳዊ የትንተና ዘዴ መሰረት የዚህን ዓለም ክስተት በቁሳዊ ትንታኔ ንድፈ-ሀሳብ ሳይንሳዊ ማጠቃለያ ነው ተብሎ እንድንቀበል የተደረገ አይደለም:: ነገር ግን ቀድሞም የነበረው ግጭትና ብሶት የወሰደው ሲሆን ወደ ቁሳዊ ፅንፍ ገልቶ እንዲወጣና ትኩረትን የሳበ እንዲሆን በመደረጉ ነው:: ፅንሰ-ሀሳቦቹ ለቁሳዊ ትንታኔን ወስደዋል:: ነገር ግን የፈለገውን ያህል ግብታዊና ደመነፍሳዊም ቢሆንና የማያረካ መሰረተ ቢስ እንኳ ቢሆን ቁሳዊነት ፍፁማዊ ነው:: ስለዚህ መለኮታዊ መሰረት ነው ብለን በር እንከፍትለትም::»*[15] ብለዋል::

በሌላ አባባል ዛሬ ላይ ይሄንን አባባል ቆም ብለን በታሪክ መሀደር ስንመለከተው ከቁሳዊ ቀኖና የአምላክን መኖር በመረጃ ካረጋገጡ ሳንቲስቶች ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖዋል:: ሳይንስም ብቸኛው ዳኛ በመሆን የአምላክ መፈለጊያ መንገድም ሆኖዋል:: እንደውም አንዳንድ ብቅ ያሉ አዝማማሚያዎችም በዩናይትድ እስቴት creationsim እና «Intellignt design». የተሰኙ የዘርፉ መጠሪዎች ሲሆኑ ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች በፈጣሪ መገኘታቸውን በሳይንሳዊ ዘዴ ማረጋገጫ ዘዴ ነው::

ይህ የሚያመለክተውም ሳይንስና ሀይማኖት ምንም የማይጠረሱ የመረጃ ምንጮች መሆናቸውን ወደ ቀድሞ ስምምነታቸው እየተመለሱ

---

15 . Richard Lewontin, "Billions and Billions of Demons", *New York Review of Books* , January 9, 1997, p. 28

መሆናቸውን ነው የምንረዳው። እንደውም ከቀድሞው የሳይንስ አመለካከት በተለየ መልኩ ሀይማኖታዊ እውነታዎች የሚረጋገጡበት ፊፅማዊ ዘዴ እየሆነም መጥቶዋል።

በሀይማኖትና በሳይንስ መካከል በተፈጠሩ አንዳንድ ቅራኔዎች መንስኤው የአንዳንድ ሀይማኖቶች ከእውነት የራቁና ኢ-ሳይንሳዊ መመሪያ ስለሚከተሉ ነው። ነገር ግን ከንደነዚህ አይነት መሰረታዊ ችግር ኢስላም ንፁህ ነው። ንፁህና እውነተኛውን የአምላክ አላህ(ሱ.ወ)[18] መለኮታዊ ራዕይ ስለሆነ ነው። እንዲሁም ኢስላም ሳይንሳዊ ግኝትን ያበረታታል። በተዘዋዋሪም ፍጥረተ-ዓለሙን ማጥናት ፈጣሪን ከመፈለጊ ዘዴም አንዱ መሆኑን ያወሳል። በዚህ ዙሪያ ላይ ቁርአን የሚከተለውን ይለናል።

«ከበለያቸው ያለውን ሰማይ እንዳች ሽንቁር የሌለው አድርገን እንዴት እንደገነባነውና እንዳስዋብነው አያዩምን? ምድርንም ዘረጋናት። ከበላይዋም ጋራዎችን አቆምን።ከውስጧም አስደሳች የሆኑ (የእጽዋት) ዓይነቶችን ሁሉ አበቀለ።ከሰማይም የተባረከ ውሃን አወረድን።በርሱም አትክልቶችንና የሚታጨዱን (አዝመራ) አበቀልን።»(ቁርአን 50:6-7-9-10)

ከላይ ባየነው የቁርአን አንቀፅ መሰረት ቁርአን ሰዎች ሁሉም እንዲመራመሩና በሚኖሩበት ዓለም ማንኛውንም ነገር በምክንያትና በምርመር እንዲያውቁ አበክሮ ይናገራል። ስለዚህ ሳይንስና ሀይማኖት ይደጋገፋሉ። ግለሰቦችንም ካለአዋቂነትና ከመሀይምነት ቀንበር ይታደጋቸዋል።

ግለሰቡ በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ እንዲያስብ ያሳስባል። አንድ ግለሰብ ለፍጥረተ-ዓለም ያለውን ምዕናባዊ እይታ ሰፋ እንዲልና የአምላክን ተአምራዊ ስራ በፍጥረተ-ዓለሙ ስሪት ላይ ማስተንተን

[18] (ሱ.ወ) አላህ ጥራት ይገባው ማለት ነው።

እንዳለበት ኢስላም ያዘዋል። ታዋቂው ፊዚገት ማዳክስ ፕላንክ እንዳሉት።

*«ማንኛውም ግለሰብ በቁም ነገር ሳይንሳዊ ምርምር ለመስራት ከፈለገ ሳይንስ ቤተ-መከራ መግቢያ በሩ ላይ ሀይማኖት ከሌለህ አትግባ! ይህ ልዩ ባሀሪ በእውነተኛና በትክክለኛ ሳይንቲስቶች ዘንድ ያለ የማይሻር ባሀሪ ነው።»*[14] ብሏዋል።

ፍጥረተ-ዓለሙ እኩቶ ከያዘው ነገር በአጋጣሚ ተብሎ የሚገለፅ ነገር አይደለም። ብዙ ሳይንቲስቶች በዚህ ታላቅ እውነታ የተሳሳተ ድምዳሚያቸውን ወደ ጎን ጥለው ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ፍጥረተ-ዓለሙን ባጤኑ ቁጥር ከአንድ እውነታ ጋር ይፋጠጣሉ። እርሱም እንከን የለሽ ስርዓት በሆነው ፍጥረተ-ዓለም ይማረካሉ። እያንዳንዱን አዳዲስ ግኝት የፍጥረትን እውነታ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ያረጋግጣል። በርካታ ቁጥር የላቸው የዘመናችን ፊዚስቶች የፍጥረትን እውነታ አፅድቀዋል። ከ21ኛው ክፍለ ዘመን ሳይንቲስቶችና አስትሮኖመርስ አንዱ የሆኑት ዴቪድ ዳርሊንግ እንደሚሉት፦

> *«አንድ ወቅት ምንም ነገር ከሌለበት ድንዘር ላይ ከዋክብትም ሆኑ የከዋብ ክምችት (galaxies) ከልነበረበት ከአንድ የልብ ምት በፊት ፍጥረተ-ዓለም (universe) መጠኑ ይህ ነው በማይባል ግዙፍ ፍንዳታ ተጀመረ። ፍንዳታውም ቁስ አካልና ሀይልን ጨምሮ በማይታሰብ ሁኔታ የአሁን ቅርፅ ያዘ። በፍጥነትም ሀዋው እየሰፋና እየተለጠጠ በመሄድ ላይ ያለው ይህ የምታዩት ፍጥረተ-ዓለም በአንድ ወቅት የአንድ ሰኮንድ አድሜ ነበረው።በመነግጠል እርስ*

14. Henry M. Morris, *Men of Science Men of God*, Master Books, 1992, p.13

*በርስ ተለያይቷል፡፡ በመጨረሻም ለዚህ ሀብር ያለው ፍጥረት በሙሉ መሰረተ-ለጥንት ሆኖዋል፡፡»*[18] ብለዋል፡፡

ብቻ ባጠቃላይ መልኩ ሁሉም ማለት ይቻላል በተለያዩ ሳይንሳዊ የጥናት ዘርፎች ላይ ያሉ መሰራቾች ለእምላክና ለመለኮታዊ መፅሐፍቱ እጅ እየሰጡ ነው፡፡ በታሪክ ውስጥ ጎልተው ከሚታወቁ ተላላቅ የፊዚክስ ሊቆች እነ ኒውተን፤ ፈራዳይ፤ ኬልቪን እና ማክስዌልን ጨምሮ በርካቶቹ ሳይንቲስቶች ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በታላቁ ፊዚገትና ሳይንቲስት አይዛክ ኒውተን ወቅት እንደሚታመነው የተለያዩ የጠፈር አካላት ፕላኔቶች የሚደርጉ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ ሕግ ነው ተብሎ ይታመን ነበር፡፡የኒውተን እምነት ግን የህዋውም ሆነ መሬት ምንጫቸውና ፈጣሪያቸው አንድ ስለሆነ የግድ አንድ አይነት ተመሳሳይ ሕግና ስርዓትን ይከተላሉ በማለት እንዲህ ብለዋል፡-

*«ይህ እጅግ በጣም ወደር የለሽና ውብ የሆነ የፀሐይ፤ የፕላኔቶችና የኮሜቶች ስርዓት በበላይነት የሚመራና የሚገዛ አንድ ወጣ ያለ ለስተኛ አካል መኖር አለበት፡፡»*[19] ብሏል፡፡

ከላይ እንዳየነው በሺዎች የሚቆጠሩ እያሌ ሳይንቲስቶች የፊዚክስ[1] የሒሳብና የስነ ክዋክብት ተመራማሪዎች ከመካከለኛው ዘመን እንስቶ ፍጥረተ-ዓለም በአንድ አሀዱ በሆነ ፈጣሪ እውን መሆኑን ያረጋግጡ ነበር፡፡ ድምደሚያቸውም አንድ ነበር፡፡

የፊዚክስና የአስትሮኖሚ ጥናት መስራች የነበረው ጆሀንስ ኬፕለር በአምላክ ላይ ጠንካራ እምነት እንዳለው ከፃፈው መፅሀፍት ቀንጭበን ስንመለከት፡-

---

15 David Darling, *Deep Time*, Bantam Press, 1989.

18. Max Planck, *Where Is Science Going?*, Allen & Unwin, 1933, p.214.

*«እኛ የሰኑ ክዋክብት ሊቆች ከሁሉም በተሻለ መልኩ በሳይንስ መፅሀፍቶቻችን የአምላክ ክፍተኛ ክሁናት ነን፡፡ በዚህ ላይ ከማንም በተሻለ ብቸኛ ባለመብት እኛው ነን፡፡ ይህም የሚሆነው ለእአምሮዎችን ክብር ለመቀዳጀት ሳይሆን ነገር ግን መሆን ያለበት ከዚህ ሁሉ የበላይ ለሆነው ፈጣሪ ክብር ሲባል ነው፡፡»*[39] ብሎዋል፡፡

ታላቁ ፊዚገት ዊሊያም ቶምሰን (ሎርድ ኬልቪን) ሙቀት ከሌሎች ሀይሎች ጋር ስላለው ግንኙነት ጥናት (Thermo Dynamics) ሊቅ ሲሆን በአምላክ መኖር የሚያምን ክርስቲያን ነበር፡፡ የዳርዊንን የዝግመተ ለውጥ ንድፈ- ሀሳብ (Evolution Theory) አጥብቆ ይቃወም ነበር፡፡ ከመሞቱ ጥቂት አስቀድሞ አንድ ነገር ተናግሮ ነበር፡፡የሕይወትን አመጣጥ በተመለከተ እንደጻፈው *«ሳይንስ የፍጥረትን ሀይል አፅድቆዋል»* ብሎ ነበር፡፡ በኦክስ ፎርድ ዩኒቨርስቲ የፊዚክስ ፕሮፌሰር የነበሩት ማቲዎስ በ1992 በሳተሙት መፅሀፍ ተመሳሳይ ሀሳብ ሰንዝሮዋል፡-

> *«የሕይወት የሚስጠራዊ መረጃ የሆነው DNA (ሀብለ ሀዋስ) የተፈጠረው በአምላክ ነው»* በማለት ደምድሞዋል፡፡ እንደርሱ አባባል *«ፅንስ ማለት ሂደቱ ወደር የለሽ አስገራሚ ትስስር ያለው ነው፡፡ ያቺ ደቂቅና ረቂቅ ውህደ-ህዋስ ሽል ትመስርታለች፡፡ሙሉ አካል ግንቢታ ሰው ታንጻለች፡፡ እንደ ሰነ-ሀይወት ግኝት መላ ሂደቱ ታአምራዊ ነው፡፡ እንዴት የሚደንቅና ውበት ያለው ውስብስብ ነገር መነሻው ቀላል ጅማሬ ኖረው? እንዴት አንዲት ነጠላ ነጥብ ወይም ከአንግሊዘኛው (i) ነጥብ በታች የሆነች ነገር ስሜት ያለው አካል ፈጠረች? ባጠቃላይ መልኩ መላ ስርዓቱና ሂደቱ ሊታሰብ*

[39] . Henry M. Morris, *Men of Science Men of God*, Master Books, 1992, p.13

*የማይቻል ትንግርት ነው:: ሕጅግ የሚያስገርም ኃያል ትይንት ነው:: ማለት ይቻላል::"*[18]ብሏል::

እንዴት የDNA ህዋስ ብቻ የምትይዘው የመረጃ ብዛት ወደ ፅሁፍ ቢገለበጥ ከዘጠኝ ኢንክይክሎፒዲያ ጥራዝ ፅሁፍ ይበልጣል::አይገርምም!

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ሳይንቲስቶች የፍጥረተ ዓለም ህልውና እውን ሊሆን የቻለው በኃያሉ ፈጣሪ ነው ብለው ካፀደቁት ውስጥ በጥቂቱ እስከ ታላላቅ ስራዎቻቸው ጋር ስንመለከት::

- ሮበርት ቦይ " (የዘመናዊ ኬሚስትሪ አባት )
- ሱና ዊሊያም ፒቲ (የዘመናዊ ኢኮኖሚና የእስታስቲክስ ሊቅ)
- ሚካኤል ፈራዳይ (በሙ-ገናና የፊዚክስ ታላቅ ሊቅ)
- ግሪጎሪ መንዴል (የጄኔቲክስ (ስነ-ዘርመል) ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘና የዘርፉ መስራችና አባት በመባል ሲታወቅ የዳርዊንን ንድፍ ሀሳብ ውድቅ ያደረገ ነው::)
- ሊዊስ ፓስተር (በባክቴሪያ ጥናት ታላቅ ሊቅ ሲሆን በዳርዊን ላይ ጦርነት አውጆዋል)
- ጆን ዳልተን (የአቶም ንድፈ-ሀሳብ አባት)
- ቢሌይስ ፓስካል (በሂሳብ ዘርፍ ጉል ስፍራ ያለው)
- ጆን ሬይ(በእንግሊዝ የተፈጥሮ ጥናት ከፍተኛ ቦታ ያለው)
- ኒኮላስ ስቴኖ (ለመጀመሪያ ግዜ የመሬትን ንብርብር ንጣፍ (stratographer) ያገኘ)
- ካርሉስ ሊኒየስ (የስነ-ህይወት መዋቅርን ለመጀመሪያ ግዜ ያገኘ)
- ጂኦርጅስ ኩቪር (የንፅፅራዊ አናቶሚ መስራች )
- ማቲዩ ማውሪ (በውቂኖስ ጥናት የታወቀ ሊቅ)

---

18. Robert Matthews, *Unraveling The Mind of God*, p.8

- ቶማስ አንደርሰን (ኦርጋኒክ ኬሚስቲሪን ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመረ)

## ተአምራኛው አካላታችን

### «እድገቱን ያልጨረሰ አይን አያይም»

አይን የሚለውን ቃል ስንሰማ በአዕምሮዋችን ጎዳ የሚመጣው ምዕናባዊ እይታ ምንድን ነው? በሕይወታችሁ እጅግ ዋና መሰረታዊ ነገር ማየት መቻል እንደሆነ ያውቃሉን? የገዛ አይናችሁን ታአምራዊ አሰራር አስባችሁም ሆነ ተናግራችሁ ታውቃላችሁን? አይን ካሉት ግንባር ቀደም ፍጥረታት ውስጥ ጉልህ ስፍራ አለው፡፡በእምሳክ መፈጠሩን ከሚጠቁሙ መረጃዎች አንዱ ነው፡ ሁሉንም ለእይታ የሚጠቅሙ አካሉች የእንስሳም ሆነ የሰው ጨምሮ በከፍተኛ ሁኔታ የተሰራ ምርጥ ዲዛይን ነው፡፡ ይህ ልዩ አካል እጅግ ወሰን የለሽ ውስብስብ ሲሆን ከተራቀቁ ሰው ሰራሽ መሳሪያዎች የላቀ ነው፡፡ የዓለማችን ቁጥር አንድ የተፈጥሮ ካሜራ ነው ቢባል ቢያንሰው እንጂ አይበዛበትም፡፡ አይን ለማየት ስርዓተ-አካላቱ በጥምረት መቀናጀት አለባቸው፡፡ ለአብነት ያህል፡- አይናችን ቅንድቡን ብቻ ቢያጣና ሌሎች የተቀሩ አካላቱ ማለትም ኮርኒያ፣ ልባስአይን ፣ መጣኒ ብርሃን፣ብሌን፣ምስሪት፣እይታዊ ድራብ ፣መሃለይ ድራብ፣ የአአይን ጡንቻ የእንባ ዕጢን ጨምሮ ለአደጋ እንደሚወድቁ እናውቃለን? ከዚህ በኋላ አይን የማየት ተግባሩ ሊቆም እንደሚችል ስንቶቻችን እናውቃለን? ሌላው ቀርቶ መላ አካላቱ ተሟልቶ የእንባ ዕጢ ስራውን ቢያቆም በፍጥነት አይናቻችን ይደርቅና ለአይነ-ስውርነት በተዳረግን፡፡

የአይናችንን ውስብስብ ስራ ብቻ ተመልክተን ሁሉ ነገር በአጋጣሚና በድንገት አሊያም በዕድል ተከስተ የተሰኙ ዘዬዎችን የሚከተለው የቁሳዊና የአዝጋሚ ለውጥ ፍልስፍና መሰረተ-ቢስ መሆኑን መረዳት እንችልምን? ይህ ማለት የአይናችን ልዩ ግኝት ከሌሎች ለየት

ባለ ሁኔታ የተከሰተ ነው ለማለት ያስችላልን? አይን ባለ ብዙ ክፍል ውስብስብ ስርዓት ነው። እነዚህ የአይን ስሪተ-አካላት በአንድ ጊዜ በድንገት ተገኙ ማለት ያስችላልን? በሌላ አባባል በዝግመተ ለውጥ (Evolution) ፅንስ ሀሳብ ያደገ አይን ያያል ማለት እንዴት ይሆናል?

ስለዚህ ይሄንን ነባራዊ እውነታ ራሳቸውም ተቀብለውታል። ለመነፃፀር ያህል አይታና የወፎቹ በረራ ሊካሄድ የሚችለው የተሟላ አይንና ክንፍ ሲኖር ነው። ግሚስ አይን አያይም እንዲሁም በግሚስ ክንፍ አይበረርም። ስለዚህ የግድ መቀበል ያለብን አንድ ነገር አለ። እርሱም የዚህ ሁሉ ጥበባዊ ኃይል ባለቤት የሆነውና ሁሉንም ሕይወት ያለውን ነገር ሕያው በማድረግ የማየትና የመስማትን ወዘተ. ስሜቶችን የዘራው አላህ ነው። በሌላኛው ጎን እንዴት ሩሃቸውን የሳቱ ማሰብ የማይችሉ ህዋሳት ወደ ማስተዋልና ማሰብ ደረጃ ደርሰው የተፈለገውን ግብ ሊመቱ ቻሉ? ማየትና መስማት የቻሉት በራሳቸው ፍላጎትና የልፋት ውጤት ነው ማለት ነው? ይህ ፍፁም የማይሆን ነገር ነው። ቁርአን እንደሚያስተምረው የመስማትና የማየት ችሮታ ፈጣሪ ለሁሉም ፍጥረታቱ ከዋለላቸው ምርጥ ፀጋ መሆኑን ያወሳል።

«የፈጠረላችሁ መስሚያ) ጆሮ (መመልከቻ) ዓይንና (ማሰቢያ) አእምሮ ያደረጋላችሁም እርሱ ነው። ግና ጥቂትም አተመሰግኑትም» በላቸው። (ቁርአን 67፤23)

## የአካላችን አፈጣጠር

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አሊያም በዩኒቨርስቲዎች ስለ ሰው አካል ስሪት ተምረናል።የሠው ልጅ አካል የአላህ ጥበብ ከተንፀባረቀባቸው ተአምራቶች አንዱ ነው።የአላህን መኖር የሚያረጋግጡ ማብቂያ የለሽ ተአምራት በውስጣዊውም ሆነ በውጫዊው አካላችን ውስጥ ይገኛሉ።

የውጫዊውን አካል አፈጣጠር በማየት ብቻ የአሳሁን ጥበብ ረቂቅነት ለመረዳት እንችላለን።የሠው ልጅ አካል የተዋቀረው በሁለት እጆች በአካልና በጭንቅላት ሲሆን ይህ አወቃቀር የተመጠነውም እጅግ በተስተካከለ ሁኔታ ነው።

ለምሳሌ የእያንዳንዱ ሰው አካል ከጭንቅላቱ ስምንት እጥፍ የሚተልቅ ሲሆን የእያንዳንዱ ሠው የፊት ርዝመት ደግሞ በአማካይ የአፍንጫውን ሶስት እጥፍ ያክላል።በሁለቱ አይኖቻችን መካከልም ያለው ርቀት የአንድ አይንን ያህል የረዘመ ነው። እንዲሁም በሁለቱ እጆቻችን እና እግሮቻችን መካከል ያለውም አመጣጠን ለሠው ልጅ እጅግ በተመቸ ሁኔታ ነው።

የሠው ልጅ አካል በምድር ላይ ካሉት ማሽኖች ሁሉ እጅግ የተሻለ ነው። እያንዳንዱ ማሽን የሠራውን ጥበብ እንደሚያሳይ ሁሉ የሠው ልጅ አካልም የፈጣሪውን ወሰን የለሽ እውቀትና ችሎታ በሚገባ የሚያሳይ ነው። የሠው ልጅ ውስጣዊ አካልም እንዲሁ ብዙ አስገራሚ ነገሮችን ይዟል። እስኪ ለአፍታ ፅንስ (Embryo) እንመልከት።

በአንድ ወቅት መነሻው ቅንጣት የስጋ ቁራጭ ነበር። ከጊዜ በኃላ የተሟላ አካል ይሆናል። ምክንያቱም የሕዋሳቱ መሰያየት መቻልና በተለያየ አካል ግንባታ የስራ ድርሻ ላይ ተሰማርተው አንድ በአንድ ህዋሳቱ እጅ፣ እግር፣ ውስጣዊ አካልና ሙሉ የደም ስራችን በመዘርጋት እርስ በርስ በመያያዝ ደረጃ በደረጃ በትጋት እኛነታችንን አስገኙ።ነገር ግን የሚገርመው በሙሉ ምንጫቸው አንድ ከሆነ ህዋስ ወደተለያዩ አካል ግንባታ መሰማራታቸው ነው። ህዋሳቱ ይህን ስራ ሲሰሩ ከሆነ ቦታ ከሚሰጣቸው ልዩ ምስጥራዊ ትዕዛዝ ተቀብለው በተሰጣቸው ፕላን መስመራቸውን ሳይስቱ ተግባራቸውን መወጣት መቻላቸው እኛን እውን ሊያደርጉ ችለዋል።

እጅግ የሚገርመው በአንድ አካል ግንባታ ላይ የተሰማሩ ሕዋሳት የርስ በርስ መተዋወቅና መቀናጀት መቻል ነው:: እንዴት እነዚህ ረቂቅ ደቂቅ የሆኑ ህዋሳት የአእምሮን ስርዓተ-ነርብን ፤አይንን ጆሮን በተናጠል ሊሰሩ ቻሉ? እንግዲህ እንዴት እነዚህ ማሰብ የማይችሉ ሩህቸውን የሳቱ ፍጥረታት ወይም የምሉኪውል ስብሳቦች የስራ ክፍፍላቸውን በየ አባላቶቻቸው ተደራጅተው ተአምራዊውን አካላታችን ገነቡ? እስከሁን መልስ ያልተገኘለት ጥያቄና በሳይንሱ መህበረሰብ ዘንድ ተአምር አሰኝቶዋል :: ከነዚህ ሞሉ ኪውሎች ረቂቅ ስራ በስተጀርባ ያለው ሀይል ማን ነው? በእውነቱ ከሆነ የዚህ ስራ አደራጅና አቀናባሪው አላህ ነው::የዓለማት ጌታ የሆነው፤መላውን ፍጥረተ-ዓለም ያስገኘው ነው::

«ይህ (መልዕክት) እውነት መሆኑ እስኪገለፅላቸው ድረስ በመላው አድማስ በነፍሶቻቸውም ውስጥ ተአምራቶቻችንን እናሳያቸዋለን:: ጌታህ በሁሉም ነገር ላይ መስካሪ መሆኑ በቂ አይደለምን» (ቁርአን 41:53)

# አካላችንን የሚከላከል ህብረ-ብሄር ጦር

## ይህንን ያውቁ ኖሮዋል?

የሰው ልጅ ካሉት ሁለት የደም ህዋሳት አንዱ ነጭ የደም ሴል ሲሆን ተግባሩም ማንኛውም ጎጂ ነገር ወደ አካላታችን ሰርጎ ገብቶ እንዳይጎዳን የመከላከያ ዘብ ነው:: የዚህ ህዋስ አባላት እኛ በሚገባን ቋንቋ በተለያዩ የጦር ሀይሉች የተደራጀና በተለያዩ ብርጌዶች የተከፋፈለ ነው፤ ትክክለኛ ድንበራቸው ቆዳችን ሲሆን ማንኛውም በአድ ነገር ወደ ቆዳ ዘልቆና ሰርጎ እንዳይገባ በተጠንቀቅ በተደራጀ መልኩ ይጠብቃሉ:: ለአብነት ያህል እንዝልና ጀርሞች አሊያም ቫይረሶች በሆነ አጋጣሚ ወደ ውስጥ ቢገቡ::

ነጭ የደም ህዋሳት በመላው አካላችን ተሰረሰጭተው ስለሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ መከላከያ እርምጃቸውን ይወስዳሉ::ይህ ጠላት ከአቅም

በላይ ከሆን ለአንጎል ተጨማሪ ግብረ-ሀይል ይጠይቃሉ:: የጠላት ሀይል በዚህ ከከሰመ የተጎዳው አካላችን ቶሎ ያገግማል:: የሞቱትም የወገን ሀይሎች (ነጭ የደም ሲሎች) በመግል መልኩ ይወገዳሉ:: የጠላት ሀይል ያየለ እንደሆነ፤ ከመጀመሪያዎቹ ብርጌዶች ውጭ ሌላ ሀይል ይሰካል:: የተለያዩ የኬሚካል ጦር መሳሪያዎችን ታጥቆ ከተፍ ይላል:: ውጊው ይጧጧፋል::

እንጎልም ስለጠላት መረጃ ይሰበስባል:: ሪፖርት በየ ግዜው ይደረግለታል አፋጣኝ መልስም ይሰጣል::ከጠላት ወረዳ አደጋው እየበረታ ከሄደ የመከላከያ ሀይሎቻችን ስልት ይቀይራሉ:: ፓጎሳይት የተባሉ ጭንብል የታጠቁና ራሳቸውን ደብቀው ለጠላት ወዳጅና አጋዥ መስለው አውደ ውጊያው ሜዳ ይዘልቃሉ:: የሚገርመው ደግሞ በቅርፅና በመጠን የተለዩና እንደልብስ መቀንጣጫና ማፍኛ ነገር ያላቸው ጠላትን በቀላሉ ለመያዝ ክሬም መስል ጣፋጭ ነገር በመቀባት፤ ጠላት ጣፋጭ ምግብ አገኘሁ ብሎ ሲሾማ በመቅፅበት ውጠው የሚያስቀሩ ናቸው:: ባመረቱት የኬሚካከል መስሪያ አፍነው የሚፈጁም ናቸው:: የተማረኩት ጠላቶች ለምርመራ ወደ አንጎል ይወሰዳሉ::

የአንጎል የደህንነት አባላት ስለጠላት በቂ ምራመራ ባለቸው ትልቅ ላብራቶሪ ጥናት ካደረጉ በኃላ፤ ጠላትን በጅምላ የሚጨርስ ፋዋሽ መድሀኒት ያመርታሉ:: የተመረተው መድሀኒት ከመደበኞቹ የመከላከያ አባላት ውጪ የሆኑ ልዩ ሀይሎች መድሀኒቱን ጦር አውድማ ድረስ የመጡትና በጠላት ወረዳ ላይ ያፈንዳሉ:: ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ጠላት ድል ይነሳል:፤ በመጨረሻም ከጠላት ጋር የተደረጉ ትግሎች በሙሉ አንጎል ውስጥ ባለ ትልቅ ለይብረሪ ወይም የመረጃ መዕከል በስርዓት ይቀመጣል:: መረጃው ስለ ጠላት ምንነትና ዓይነት የተመረተው የመድሀኒት አይነት በሙሉ አንድም ሳይቀር ይመዘገባል:: ምክኒያቱም ጠላት በድጋሚ ቢከሰት እንኳ አዕምሮ በቂ መረጃ ስላለው ወድያውኑ

እርምጃ ይወስዳል። ስለዚህ አካላታችን በንደነዚህ አይነት ትጉና ታታሪ በሆኑ የመከላከያ ስርዓተ-መዋቀር የተጠበቀ መሆኑ አይገርምም።

ስንቶቻችን ነን በገዛ አካላታችን ውስጥ ጠንካራ የተደራጀ ዲሲፕሊንድ የሆነ መከላከያ ሀይል እንዳለን የምናውቀው? ስንቶቻችን ነን በበሽታ አምጪ ተህዋሲያን በምንተነፍሰው አየር ፤በምንበላው፣ በመንጠጣውና በምንነካው ነገር ዙሪያችንን እንደከበቡን የምነውቀው? ስርገው ከገቡ ለከባድ ህመም አሊያም ለሞት እንደሚዳርጉን የምናውቀው? ሰውየው አወቀም አላወቀም በትጋትና በርብርብ ህይወቱን ለማዳን ብሎም ለመፈወስ ከሞት ለመታደግ ይታገላሉ። ሰብአዊ ፍጡር በሽታን የመከላከል ሥርዓት ለጥቂት ሰዓታት ቢነፈገው ኑሮ የመኖር ህልውናው ለአደጋ በተጋለጠ ነበር። ስለዚህ የአላችን መላ ስርዓተ-ፍጥረት ተሟልቶ በአንዴ መገኘቱን ያሳያል። ባጠቃላይ የዚህ ከያኒና ቀማሪ ባለቤት የሆነውን አላህን የስረዱናል።

## የሰው ልጅ አእምሮ

የሠው ልጅ አእምሮ በአማካይ 10 ቢሊየን የአእምሮ ህዋሶችን (ኒውሮን ሴሎችን) በውስጡ ይይዛል። እነዚህ ሴሎች (ህዋሶች) ደግሞ እርስ በእርስ በ100 ትሪሊየን ጥልፍልፍ መስመሮች ይገናኛሉ። አእምሮዋችን ይህ ነው የማይባል ምስጥራዊ ስራት አለው። በዛኑ ልክ ስራውም እጅግ የተወሳሰበ ነው። በመላ ሰውነታችን በተዘረጋው የመረጃ መረብ በመታገዝ ከአካባቢያችን ጋር በሰላም ያለምንም ችግር እንድንኖር አስችሎናል። በእነዚህ የግንኙነት መስመሮች ውስጥ ወደ አእምሮ እና ከአእምሮ የሚተላለፉ መልእክቶች እጅግ በጣም ፈጣን በሆነ መልኩ በሠአት 320 ኪ.ሜ ይጓዛሉ። በአእምሮና በቀሪው ሰውነታችን መካከል ያሉት ነርቮች መልእክትን ለመለዋወጥ ልክ እንደዋናንዳና በመሆን ያገለግላሉ።

በአጭሩ ሰውነታችን በእያንዳንዷ ደቂቃና ቅፅበት እጅግ ከፍተኛ የትራፊክ እንቅስቃሴን ያስተናግዳል ማለት ነው።በአንዲት ነጠላ ሰከንድ ውስጥ ብቻ በሺ የሚቆጠሩ መልእክቶች በተናጠል በአእምሮና በቀሪው የአካል ክፍል መካከል ይመላለሳሉ።በአንዲት ደቂቃ ውስጥ ብቻ ከመቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊየን የሚደርሱ ኬሚካላዊ ለውጦች በአእምሮአችን ውስጥ ይካሄዳሉ። ሌላው ቀርቶ ይህንን መፃህፍ በሚያነቡበት ወቅት እንኳን በእያንዳንዷ ሰከንድ አንድ ሺኛ ጊዜ ውስጥ በሰውነታዎ ጡንቻዎችና በአእምሮዎ መካከል በመቶ የሚቆጠሩ የመልእክት ልውውጦች ተደርገዋል።

እነኚህ መልእክቶች ሲያነቡ መረጃ ከማቀበል ባለፈ ወንበርዎ ላይ ደገፍ ማለትዎን፡ የያነቡትን ነገር መረዳትዎን፡ የልብዎን ምት፡ እስትንፋስዎን፡ የአይንዎን መርገብገብ ፡ የፀጉርዎን ማደግ፡ የአፍንጫዎን ማሽተትና የጆሮዎን መስማት የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ።ከእነዚህ ድርጊቶች ውስጥ አንዱን እንኳን በቅጡ ለመረዳት ቢሞክሩ እጅግ ብዙ ገፅ የኬሚካል ቀመሮችን መፃፍ ይኖርብዎታል። በዚህ ቀመር ውስጥ ደግሞ አንዷ እንኳን ብትሣሣት የሰውነትን ሚዛን ልታሣጣ ትችላለች። ይህ የሚዛን መዛባት ፀጉርዎን ሲያበጥሩ በድንገት እጆዎችን እና አይንዎን በማበጠሪያው እንዲወጉ ሲያደርግዎ ወይም ሲራመዱ ተንገዳግደው እንዲወድቁ ሊያደርግዎ ይችላል።

የአእምሮችንን የህዋሳት ብዛትና የርስበርስ መያያዣ ስርዓት በምሳሌ ብንመለከት።የእንግሊዝን 13 እጥፍ የሚሆን ግዙፍ ቦታ እንዳለ እናስብ።ይህ ቦታ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በዛፍ የተሞላ እንደሆነና እያንዳንዱ ዛፍ ደግሞ 10000 ቅጠሎች እንዳሉት እንቁጠር። እንግዲህ የእነዚህ ቅጠሎች ድምር የአእምሮ ሴሎች ከሚገናኙባቸው መስመሮች ጋር እኩል ነው ማለት ነው። በሌላ አባባል ከምፒውተር የአዕምሮዋችን ታምሳሌት ነው ይባላል።አንድ ከምፒውተር ቢበላሽ በአንዲት ክፍል

ውስጥ ፊታተን ዘረጋግተን እንሰራዋለን፡፤ ነገር ግን የአንድ ሰው አዕምሮ የመበላሽ ዕድል ቢገጥመውና እንደ ኮምፒውተር ፊታታን እንሰራው ብንል እንግሊዝን 13 ጊዜ የሚሰፋ ክልል አይበቃውም ቢባል ታምናላችሁ? አይገርምም! ታዲያ የዚህ ውስብስብ ዲዛይንና ምህንድስና ባለቤት ማነው? ወይስ እንደሚባለው ባጋጣሚ የተከሰተ ዱብዳ ነው፡፡ ፍርዱን ለናንተው፡፡

ነገር ግን አላህ የሠውን ልጅ እጅግ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ከመፍጠሩ የተነሣ እጅግ ውስብስብ ስራዎችን እንኳን ያለ እንከን መስራት እንዲችል አድርጎታል፡፡ ለዚህ ውለታውም እናመሰግነው ዘንድ በእርግጥም ይጠበቅብናል፡፡

## የሠው ልጅ አጥንትና ድንቃድንቆቹ

የሠው ልጅ አጥንት እንከን የለሽ ንድፍን ያካተተና 206 አጥንቶችን አሣክቶ የያዘ እጅግ ድንቅ የጥበብ ስራ ነው፡፡ እነዚህን የተሠካኩ አጥንቶችን በመጠቀምም የሠው ልጅ ለየት ያሉና ከባድ እንቅስቃሴዎችን ለመፈፀም ይችላል፡፡በቅርብ አመታት ውስጥ እንኳን በሳይንቲስቶችና በመሀንዲሶች በከፍተኛ ጥናት የተፈበረኩት ሮቦቶች የሠው እጅ ያለውን የብቃት ደረጃ ሊደርሡ ቀርቶ ተቀራራቢ ሙከራ እንኳን ማግኘት ተስኗቸዋል፡፡

በጥምረት የሠውን ልጅ የሚገነቡትን አጥንቶች በተናጠል ስናስተውል ምን አይነት እንከን የለሽ ንድፍ እንዳለው እንረዳለን፡፡ከዘመናዊው ቴክኖሎጂ ውጤቶች መካከል አንድ ምሣሌን ወስደን ለማየት እንችላለን፡፡ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ረጃጅም ህንፃዎችን ለመገንባት ጥቅም ላይ የሚውለው ፑንቲ ሲሆን ይህም ቃል የሚወክለው በህንፃው ዙሪያ ለመንጠላጠያነት የሚገነቡትን ጥልፍልፍ የብረት መሠላሎች ነው፡፡መሠላሎቹ በሙሉ እርስ በእርስ የተሠካኩ

በመሆናቸው በህንፃው ዙሪያ ለሚሠሩት ስራዎችና ለእርማታ ስራው ድጋፍ ሆነው ያገለግላሉ፡፡በተጨማሪም የተወሳሰቡ የኮምፒውተር ስሌቶችን በመጠቀም ዘመናዊ ህንፃዎች የተሻለ ጥንካሬ እንዲኖራቸው ለማድረግ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ውስጣዊው የአጥንታችን አወቃቀር ሊወዳደር በማይችል ሁኔታ ከዚህ ሰው ሠራሽ ስርአት የላቀ ውስብስብነትን ይዟል፡፡

በዚህ ለየት ያለ አወቃቀር ምክንያት አጥንቶቻችን እጅግ የተሻለ የጥንካሬ ደረጃ መኖር ብቻ ሳይሆን ለአጠቃቀምም እጅግ ምቹ ስፋትን ያጣመሩ ሊሆኑ ችለዋል፡፡የሠው ልጅ በእርግጥም የፈጣሪው ውጤት መሆኑን ከሚያረጋግጡት ማስረጃዎች አንዩአጥንቶች መገጣጠሚያዎች ናቸው፡፡ በተለይ ሠብቃ የሚበዛባቸው መገጣጠሚያዎች ስስና ጠንካራ በሆንና ቀዳዳዎች ባሉት ስጋ መሰል አያያዥ የተያያዙ ናቸው፡፡ ከዚህ አያያዥ ስር ደግሞ የማለስለሻ ቅባት ያለ ሲሆን አጥንቱ ሲታጠፍና ማያያዣውን ስጋ መሠል ነገር ሲጨምቀው ዘይቱ በመውጣት መገጣጠሚያውን ያለሠልሠዋል፡፡ የሠው ልጆችም በዚህ ድንቅ አፈጣጠራቸው ምክንያት በአይነትም ሆነ በብዛት የተለያዩ ተግባሮችን ለመፈፀም ችለዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ድንቃድንቆች የሚያሣዩት የሠው ልጆች አካል የእንከን የለሽ ጥበብ ውጤት መሆናቸውን ነው፡፡ የዚህ ጥበብ ባለቤት ደግሞ አላህ ነው፡፡

በቁርአን ውስጥ አላህ አንድን እውነታ አናስተንትን ዘንድ እንዲህ ይለናል፡ «አፅሞችዋን እንዴት እንደምናስነሳቸውና እንዴትስ ስጋ እንደምናለብሳቸው ተመልከት» (ቁርአን 5፡ 259)

# እንስሳትና እፅዋት

## የፍጥረታቶች ብዛትና መለያየት

በሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳትና የእፅዋት አይነት በአለማችን ላይ ተንሰራፍተው ይኖራሉ። የሁለቱ ፍጥረታት ህብር ስርቶ መኖር፤ የአምላክን መኖር ያረጋግጣሉ። ሁሉም የተለየ ስርዓተ-አካል ከጠላት የመከላከል ታክቲክ ወጠ የሆነ የአመጋገብ ሥርዓት ያላቸውና አስደናቂ የእርባታ ዘዴ ባጠቃላይ ሁሉንም በዝርዝር ለማስፈር እያሌ የኢስይክሎፒዲያ ቮልዩም አይበቃንም። ለእብነት የተወሰኑትን ወስደን ብናጤን ህይወት በመሬት ላይ በድንገት ተገኘ ለማለት እንደበታችን ያጥራዋል።

በአለማችን ውስጥ በየትኛውም ቦታ ሁሉ ህይወት ያላቸውን ነገሮች እናገኛለን። ከሚሊየን አይነት በላይ የተለያዩ ፍጥረቶችን በምድር ውስጥና ላይ የምናገኝ ሲሆን ይህም ባለ ነጠላ የደም ህዋስ ፍጥረቶችን፡ ነፍሳቶችን ፣ የባህር ውስጥ ነዋሪዎችን፣ ተክሎችንና እንስሣቶችን ያካትታል።ከነዚህ ፍጥረቶች ውስጥ አንዳቸውም በራሣቸው ውሳኔና ጥረት ወደዚህች ምድር አልመጡም።ሁሉም እጅግ የተወሳሰበ አካላዊ ስርአት ያላቸው ሲሆን የፈጠራቸው ደግሞ አላህ ነው።አላህ እነዚህን የተለያዩ ፍጥረታት እንዴት እንደፈጠረ ቁርአን በሚከተለው መልኩ ይነግረናል።

«አላህ እንስሳትን ሁሉ ከውሃ ፈጠረ።ከነርሱ ውስጥ በሆዱ የሚሣብ አለ። በሁለት እግሮቹም የሚጓዝ አለ።በአራት እግሮቹ የሚጓዝም አለ። አላህ የሚሻውን ይፈጥራል። አላህ ሁሉንም ነገር ቻይ ነው» (ቁርአን 26:45)

## የንስር ዓይንና አስገራሚ ባህሪው

ንስሮች ከሺ ኪሎሜትሮች በላይ ከፍ ብለው መብረር የሚችሉ የወፍ ዝርያዎች ሲሆኑ እታች ያለው መሬት ላይ እየተካሄደ ያለውን

ዝርዝር ነገር ሁሉ ማየት የሚያስችሉ አይኖች አሏቸው፡፡የንስር አይን በ300 ዲግሪ ዙሪያውን መቃኘት የሚችል አፈጣጠር ሲኖረው የሚያየውን ነገር እንዳስፈለገው ከ6 እስከ ስምንት እጥፍ ድረስ የማተለቅና የማጉላት ችሎታ አለው፡፡ ከ4300 ሜትሮች ከፍታ ላይ በመብረር 30 ሺህ ሄክታር መሬትን ዙሪያውን መቃኘት ይችላል፡፡ ምግባቸውን ለመፈለግ ከ1500 ሜትር ከፍታ ላይ እየበረሩ እጅግ ትንሽ የሆነችን እንቅስቃሴም ሆነ የከለር ለውጥ ለመለየት ይችላሉ፡፡

ንስሮች ይህንን አስገራሚ የማየት ችሎታ ሊጎናጸፉ የቻሉት ብርሀንን ተቀብሎ ማስተላለፍ የሚችሉት የአይኖቻቸው ሴሎች እጅግ ብዙ ስለሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሴሎች ብርሃኑን ወደ አእምሮ ተቀብለው የሚያስተላልፉ ሲሆን ከሠው ልጅ ሴሎች ጋር ሲወዳደሩ እጅግ ብዛት አላቸው፡፡ እንግዲህ ይህ የብዛት ልዩነት ነው ይህንን ድንቅ የማየት ችሎታ ሊፈጥር የቻለው፡፡ንስሮች ይህንን ተአምረኛ አይናቸውን በመጠቀም ምግባቸውን ያድናሉ፡፡ ነገር ግን የዚህ ታላቅ ጥበብ ምንጩ እራሳቸው ንስሮች ሳይሆኑ ሁሉን አዋምሮ የሚፈጥረው አላህ ነው፡፡ ይህንንም እውነታ በቁርአኑ ውስጥ እንደሚከተለው ገልጾታል፡-

«አንዲትም ተንቀሣቃሽ ፍጡር የለችም በርሡ ቁጥጥር ስር ብትሆን እንጂ፡፡» (ቁርአን 23፡ 56)

## የተመጣጠነ ክንፍ

የቢራቢሮዎን ክንፍ ልብ ብለን ስንመለከት፡፡ እጅግ ባማረ ሁኔታ የተመጣጠነና ብዙ ተአምር ያቀፈ ነው፡፡ ይህ ዳንቴል መሰል ክንፋቸው በውበት አሸብርቆና ተቆጥቅጦ እናየዋለን፡፡ በግራ ፣ በቀኝ ያለው የህብረ ቀለማት ንድፍ ውበት ያለው ፀዳል አላብሰዋቸዋል፡፡ ውስብስብነቱን ለጊዜው ወደጎን እንተወውና፡፡ በሁለቱም ክንፎች ያሉትን አንድ ነጥብ ብናጤን፤እንከን የለሽ ስርዓተ መዋቅርና ሚዛናዊ መመጣጠን

እንኖዕፎዎቸዋል። በተጨማሪም የክንፎቹ ቀለማት አንዱ ከሌላው አይደባለቅም። ራሳቸውን ችለው የተቀረፁ ክንፎች ናቸው። አንዱ በአንድ ላይ የተደራረበ ረቂቅ መስፈርት የተከተለና ያሸበረቀ ሕብረ ቀለም አላቸው። በእጃችን በትንሹ ብንነካው በቀላሉ የሚበተን ረቂቅ መስፈርት ያለው አስገራሚ ነገር ነው። ወዲው ራሱን የመመሰስ ባህሪ ያለወ ነው። ቅንጣት ታክል ከክንፉ ቢወገድ ተፈጥሮዎዊ ውበታቸውን ይጋፋቸዋል። አሊያም ስርዓታቸውን ያዛባባቸዋል። ነገር ግን ስርዓተ የለሽ የቢራቢሮ ክንፍ በዓለም ላይ ማግኘት አንችልም። እቻ በሌለው አርቲስት የተሰራ የሚመስል ግርማ ሞገስ ያለው የክንፍ መረብ አላቸው። በርግጥም ያለጥርጥር በጥበበኛው አምላክ የተሰሩና የተነደፉ ስራዎች ናቸው።

## እንገተ-ረጅሙ እንስሳ

ቀጭኔዎች ብዙ አስደናቂ ገፅታዎች አሏቸው። አንገታቸው ረጅም አከርካሪ ያለው ነው። በአንገት ርዝማኔው ማንም የማይወዳደረው ቀጭኔ አስገራሚ ተፈጥሮዎዊ በህሪውን ስንመለከት።፡ ልዩ የደም ስርጭት አላቸው። ረጅሙን አንገት አልፎ ወደ አንጎል የሚዘልቀው የዘውር ደም ስርዓት ነው። ስለዚህ ጉዳይ ትንሽ ብንስብ ደም እንዴት ረጅም ከፍታ እንደሚወጣና ምን ያክል አስቸጋሪ መሆኑን ይጠቁመናል።

ነገር ግን ቀጭኔዎች ያለምንም ችግር ሊኖሩ ችለዋል። የልባቸው አደረጃጀት ሀላፊነቱን መወጣት በሚችልበት መልኩ የተደራጀ ሲሆን ያለምንም እንከንና ትግል እንዲኖሩ አስችሉዋቸዋል። ለአብነት ያህል ረጅሙን አንገት ወደታች አቀርቅረው ውሀ ሲጠጡ ይፈጠር የነበረውን አደጋ ስናስብ ውሃ ለመጠጣት ባቀረቀሩ ቁጥር የሞት አደጋ በተጋረጠባቸው ነበር። የአንገታቸው እንከን የለሽ ስርዓት ከሀይለኛ የደም ግፊት አደጋ ተድነዋቸዋል። ወደ መሬት ሲያቀረቅሩ የአንገት ላይ የደም ቧንቧ (vessele) ይዘጋና ወደ አንጎል የሚፈሰውን ከፍተኛ መጠን የለው ደም ያግዳል። ያለጥርጥር ቀጭኔዎች እኔን ሥርነተ-መዋቅር

እንደሚያስፈልጋቸው አውቀው ያገኙት ራሳቸውን ፕላን በማድረግ እንዳልሆነ እሙን ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ተሰጦ በአዘጋሚ ለውጥ ንድፈ-ሀሳብ (Evolution) መሰረት በአጋጣሚና በዝግመተ-ለውጥ ሂደት ተገኘ ማለት ፍፅም እብደት ነው፡፡

ቀጭኔዎች በሕይወት ለመኖር ይህ ዋና የዘውረ-ደም ስርዓት ወደ አንጎል የሚፈሰውን ደም ለመቆጣጠር የሚያገለግለው የደም ቧንቧ ለደቂቃዎች መቋረጥ ብዙ አደጋዎችን ጨምሮ እስከ ሞት ሊያደርስ የሚችል መሆኑን መዘንጋት የለበትም፡፡ስለዚህ ቀጭኔዎች በመሬት ላይ ለመኖር ከጀመሩበት ሰዓት አንስቶ ይህ ዋና ስርዓት አብሮዋቸው የተፈጠረ መሆኑን እንረዳለን፡፡ መጀመሪያ ያልኖረ-ነገር ከግኘቱ በኃላ ለራሱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን እየሟላ ሄደ ለማለት በጭራሽ የማይሆን ነገር ነው፡፡ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ቀጭኔዎች በዚህ ስርዓታቸው ብልህታኛውን ፈጣሪያቸውን ይጠቁማሉ፡፡ እሄንን ስርዓት አለህ አብሮ ያጎናፀፋቸው መሆኑን እንረዳለን፡፡

## የአስገራሚዎቹ ጎጆ

በበረሃ ላይ ምስጦች ቤታቸውን ሲያንፁ በግንባታቸው ከመደነቅ በቀር ማንም አልረዳቸውም፡፡ምስጦች እጅግ ረቂቅ የምህንድስና ጥበብ አላቸው፡፡ ከ5-6 ሜትር የሚደርስ ቤት ያንፃሉ፡፡ የምስጦችን መጠን ከጎጆዋቸው ጋር ስናነፃፅር ምስጦች የጎጆዋቸውን ግንባታ ከ300 ጊዜ የሚተልቃቸውን ቤት ያንፃሉ፡፡ የሚደንቀው ነገር ምስጦች ጎጆዋቸውን ሲያንፁ አይነ-ስውር ናቸው፡፡

አይነ-ስውር በሆኑ ምስጦች የተገነባው ግዙፍ ጎጆ አይቶ የማያውቅ ሰው፡- ይህ ጎጆ የተሰራው በአሸዋ ቁልልና ክምር ነው፡፡ ብሎ ሊያምን ይችላል፡፡ ነገር ግን ጎጆዋቸውን ልብ ብለን ስናይ አስገራሚ ዲዛይን እንዳለውና ፍፅም በነርሱ አቅምና ችሎ ተገነባ ለማለት ይከብዳል፡፡

የጎጆው ውስጣዊ መተላለፊያ፣ መንገዶች፣ ኮሪደሮች፣ አየር መስተላለፊያ ቬንቲሌሽን፣ እጭ መፈልፈያ ምቹ ክፍሎች ያካተተ ግንባታ ነው።

በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አይነ-ስውር ሰዎችን ሰብስበን ለቤት ግንባ የሚያገለግል ቁሳቁስ አሟልተን ብንሰጣቸውና የሚሰሩልንን ቤት ምን አይነት ቤት እንደሆነ አስበን ከምስጦቹ ጎጆ ጋር እናነፃፅር።አስቡበት፣ እንዴት ምስጦች 1-2 ሴ.ሜ ብለው ሊለኩ ቻሉ? ምህንድስናውን እንዴት ሊያገኙ ቻሉ? እንዴት በሺዎች የሚቆጠሩ አይነስውር ምስጦች በቅንጅትና በህብረት እርስ በርስ ተናበው የሚደነቅ ቤት ገነቡ?

የምስጦችን ጎጆ የመጀመሪያውን የግንባታ ደረጃ ለሁለት ብንክፍለውና መልሰን ብንገጥመው። ቀድሞ የነበሩ መተላለፊያ መንገዶች በፊት እንደነበረው ይገጥማል። እንደነዚህ አይነት ተአምራዊ ክስተት እንዴ አድርገን ነው የምንገልፀው? ከላይ ሳየነው ምሳሌ የምንስጠው ብያኔ አምላክ ሁሉንም ነፍሳት በልዩ ሁኔታና መኖር በሚቹሉበት መልክ ያመቻቸላቸው መሆኑን እናረጋግጣለን።የምስጦችን ጎጆ ብቻ ተመልክተን አምላክን ለማወቅ በቂ ምክኒያት አይሆንም?

## የተለያዩ ነገሮችን በመምሰል ራስን የመከላከል ብቃት

አንድ አንድ እንስሳት ራስን የመከላከያ ልዩ እስትራቴጂ አላቸው። አንዳንዶቹ በአካላቸው ልዩ መዋቀርና በቀለማቸው አማካኝነት ከአካባቢያቸው ጋር ፍፁም የመመሳሰል ባህሪ አላቸው።ለጠላት በማይለይ መልኩ ወዲያውኑ የቦታውን ገፅታና ቀለም ይወርሳሉ። ይህ ቴክኒክ በክፍለ ዘመናችን ያለው የሚሊተሪ ሳይንስ እንኳን ሳይቀር ይጠቀምበታል። ጠላትን ለመዳምሰስ አካባቢን የመምሰልና ትኩረትን ሰርቆ በድንገት ለመውረር የሚያገለግል የጦር ስልትም ነው።ታዲያ በዚህ ስልት ሕልውናቸውን ከጠላቶቻቸው የሚታደጉ በርካታ ፍጥረታት

በትዕበት መንነታቸውን ለውረው በዙሪያቸው ካለው ቅጠል ድንጋይ እሾዋ ወዘተ...ተመሳስለው ቁጭ ይላሉ:: እነዚህ ረቂቅ ፍጥረታት እውን ይሄንን ቴክኒክ ራሳቸው ለሩት ማለት ይቻላልን ? ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል ዙሪያቸውን የመምሰል ችሎታ ከየት አገኙ? አካባቢን መስሎ ራስን መከላከል እጅግ የሚመስጥ ራስን ከጠላት የመከላከያ ታክቲክ በልዩ ሁኔታ በፈጣሪ የተከሸነና ፕላን የተደረገ አይመስላችሁም? መልሱን ለህሊናችሁ::

# ማጠቃለያ

ያለምንም ጥያቄ ከሰው ልጅ መፈጠር የሚሻልና ሰው ፈጣሪውን ከማወቅ በላይ የሚበልጥ ነገር የለም:: በዚህች አጭር መፅሀፍ ለማንሳት የተሞከረውም እሄንን ወደር የለሽ ዕድል ለሁሉም ሰብአዊ ፍጡር በተሻለ መልኩ እንዲጠቀም ለማስቻል የተደረገ ሙከራ ነው:: እዚጋ ለአንባቢያን አንድ ነገር ለማስታወስ ያክል፡- አንድ ግለሰብ ስለ ፍጥረተ-ዓለም ግለሰቡንም ጨምሮ መፈጠሩን ለመገንዘብ ባለ ብዙ ገጽ መፅሀፍ ወይም መረጃ አያሻውም:: ገና ክፉና ደጉን መለየት ከጀመረበት ሰአት አንስቶ ማንኛውም ግለሰብ በምክንያትና በተፈጥሮው ማንም ሳያዘው የሚረዳው ገሀዳዊ ሀቅ ነው:: ማንኛውም ሰው በየትኛውም ዓለም ጊዜ፤ ዘር፤ ሀብት፤ እውቀት፤ ቀለም፤አስተሳሰብ ቢኖር እንኳ ለመረዳት የማይሳነው ተፈጥሮዋዊ ጥያቄ ነው::

ለዚህ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነን የነብዩ ኢብራሂም ታሪክ ነው :: እውነትን ለማግኘት የከፈለውን መስዕዋት:: ያደረገውን ፍጥጫ ቁርአን ዘግቦት ይገኛል:: ነብዩ ኢብራሂም የነበሩበት መህበረሰብ በእውነተኛው አምላክ የማያምንና ጣኦታትን ጠርቦ የሚገዛ ህብረተሰብ ነበር:: ኢብራሂምም ስለ እውነተኛው ፈጣሪ መኖር ምንም የመማር እድል አላገኘም ነበር:: ነገር ግን እጅ እግሩን አጣጥፎ አልተቀመጠም:: በል እንደውም ገና በለጋ ዕድሜው በምክኒያት ነባራዊውን ሁኔታ በማጤን ፈጣሪውን መፈለግ ጀመረ:: የለጥርጥር አምላክ እርሱን እንደፈጠረው ተረዳ:: ሰማያትና ምድር የርሱ ፍጥረታት መሆናቸውን በምርምር እንደረሰበት ቁርአን ታሪኩን ሲያወሳ

«ሌሊቱ በጽልመቱ በሸፈነው ጊዜ አንዲት ኮከብ አየ «ይህ ጌታዬ ነው» አለም ::(ኮከቡ) በጠለቀ ጊዜም ጠላቂዎችን አልወድም» አለ::ጨረቃንም ደምቃ ባየ ጊዜ :- «ይህ ጌታዬ ነው» አለ በጠለቀች ጊዜም :-«ጌታዬ

ቅኑን ጎዳና ካልመራኝ መንገድ ከሳቱ ሰዎች እሆናለሁ» አለ:: ፀሀይንም ደምቃ ባየ ጊዜ:- «ይህ ከሁሉም የላቀው ጌታዬ ነው» አለ:: በጠለቀች ጊዜም :- «ወገኖቼ ሆይ እኔ እናንተ ከምታመልኩት የጠራሁ ነኝ» አለ:: (13:76-78)

የነብዩ አብረሀምን ተምሳሌት ሁሉም ሰው ገቢራዊ ማድረግ ያለበት እጅግ አስፈላጊ ተሞክሮ ነው:: ይሄንን አስገራሚ ስርዓትና ፕላን የማይቀበል ስን-ምግባር የጎደለውና እብሪተኛ ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

የለመንገራገር የአምላክን መኖር የሚክድ:: ራሱንም ጨምሮ ከፊት ለፊቱ የተጋረጠውን እያሌ ምልክት ሽምጥጥ አድርጎ የካደና ለፈጣሪ እጅ ያልሰጠ ምክኒያታዊ አመለካከቱ የተኮላሸ ከንቱ ኪሳራ ላይ ያለ ሰው ነው:: ቁርአን እንደሚከተለው አውስቶታል::
«መገረም ካለብህ ከምንም ነገር በላይ እጅግ የሚያስገርመው (ከሐዲያን) «አፈር ከሆንን በኋላ እንዳ አዲስ እንፈጠራለን?» ማለታቸው ነው:: እነዚህ (ይህን ያሉት) ከጌታቸው የካዱት ናቸው:: እነርሱ በእርግጥም ከአንገቶቻቸው:: እነርሱ በእርግጥም የእሳት ሰዎች ናቸው:: ከውስጧ ዝንተ ዓለም ይኖራሉ» (ቁርአን 13:5)

ምገቢህች መጽሀፍ የተነሱ አንኳር ሀሳቦች ህይወትዎን መስመር ለማስያዝ ከማንኛውም ነገር የተሻሉ እድሉች ናቸው:: ምናልባትም በዚህ መሰረታዊ አጀንዳ ብዙ ወደ ኃላ ቀርተው ሊሆን ይችላል:: እሲያም ከዚህ በፊት እንደዚህ አይነት አመለካከት ላይኖር ይችል ይሆናል:: አሁን በዚህ እድል ተጠቀሙበት:: ለአምላክዎ እውቅና በመስጠት ላይ እርግጠኛ ይሁኑ:: እርሱም እርሶንም የፈጠረ ነው:: ከምንም በፊት አስቸኳይ ነገር ስለሆነ በዚህ ላይ በርቱ:: ምን ያክል ለህይወቶ ዋስ እንደሆነ አስቡ:: በዚህች ዓለም ሲኖሩ ልዩ በሆነ ሁኔታ እያንዳንዱ ዝርዝር ነገር በብልሀት ፕላን ተደርጎሎታል:: በዚህ ሂደት ውስጥ ምንም ድርሻ አልነበሮትም:: ይሄንን ሁሉ ትዕይንት አንድ ቀን አይኖን ከፍተው ወሰን በሌለው ፀጋ

ውስጥ ተከበው ራሳን አገኙት::የማየት፣ የመስማትና የመረዳት ፀጋ እምላኩ ለርሰ የዋለሉ ወሰን የለሽ ፀጋ መሆኑን ይነግርታል::

«አላህ ከናቶቻችሁ ሆደ ውስጥ ምንም ነገር የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ:: ታመሰግኑትም ዘንድ መስሚያ(ጆሮ) መመልከቻ(ዓይን) እና ማስበያ (አዕምሮ) ለገላችሁ ::» (ቁርአን 16:78)

ጥቅሱ እንደሚያስረዳን በእጃችን ያለውን ዝርዝር ነገር፣ የምንኖርበትን ፍጥረተ-ዓለም ጨምሮ የፈጣሪ ነው:: ስለዚህ ለርሱ ብቻ ሁለመናዎን ማስገዛትና እጅ መስጠት ለዋለሉ መልካም ነገር ሁሉ ክብርና ምስጋናን ሊቸሩት ይገባል:: ከዚህ በተቃራኒ ከሆኑ ውጤቱ ክብር ማጣት፣ ውርደትና ቅጣትን መከናነብ ይሆናል:: ከዚህ ኪሳራ አላህ ይጠብቀን:: አሚን!

የአላህ ፈቃድ ሁል ጊዜም ዘውታሪ ነው:: እርሱ ለመኖሩና ከምንም ነገር የበለጠ የቀረበ መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ ::

እርሰም ስራዎትን ይሰሩ እርሱም ሰሚና ተመልካች ነው:: አንድ ነገር አትሸሽገውም::እውቀቱ ፍጥረተ-ዓለሙን የቀደመና ያካበበ፣ በሙሉ ለርሱ ትዕዛዝ በማደር እጅ የሰጠ ነው:: ስለዚህ ሁለመናዎን የርሱ አድርጉት ወደርሱ ተጠጉ ወደርሱም ይሸሹ:: እርሱ ሁሌም ከርሶ ጋር ነውና!

**«አምላካችን ሆይ ከጎደሉ ባህሪያት እናጠራሃለን::አንተ ካስተማርከን ውጭ ሌላ ዕውቀት የለንም አንተ ዐዋቂ ጥበበኛ አምላክ ነህ» አሉ::(ሱረቱል አል በቀራ 32**